# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 048 ጥቅምት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




# በዞኑ ከ200 ሺህ ሄክታር በላይ የለማ የስንዴ ሰብል እየተሰበሰበ ነው

## - ስምንት መቶ ሺህ ኩንታል ለውጪ ገበያ ይቀርባል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- በምሥራቅ ሸዋ ዞን ከሁለት መቶ ሺህ ሄክታር በላይ በሆነ መሬት ላይ የለማ የስንዴ ሰብል እየተሰበሰበ መሆኑንና ከዚህም 6 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል ይሰበሰባል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተገለጸ። ከሚሰበሰበው ምርት 800 ሺህ ኩንታሉ ለውጭ ገበያ እንደሚቀርብም አስታውቋል፡፡

በዞኑ በበጋው የመስኖ ስንዴ ልማትም ከሁለት መቶ ሺህ ሄክታር በላይ መሬት እንደሚለማ የተገለጸ ሲሆን የመጀመሪያው ዙር የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በቦራ ወረዳ ተጀምሯል።

የዞኑ ዋና አስተዳደሪ አቶ አባቡ ዋቆ እንዳስታወቁት አርሶ አደሩ ቀደም ሲል በክረምት እርሻ ብቻ ተገድቦ የቆየ ሲሆን አሁን መንግሥት በጀመረው ከፍተኛ እንቅስቃሴ በርካታ አርሶ አደሮች ከመኸር እርሻ ባሻገር በበጋ ወቅት ወደ መስኖ ልማት እንዲገቡ እየተደረገ ነው፡፡

ሀገራችን በምግብ እህል እራሷን እንድትችል እና ከውጪ የምታስገባውን የስንዴና መሰል ምርቶችን በማቆምና በመቀነስ በሀገር ውስጥ ምርት ከመተካት አልፎ ምርቶችንም ወደ ውጪ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ለማስገኘት ጥረት እየተደረገ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አባቡ፤ ዞኑም የበኩሉን ድርሻ እንደሚወጣም አስረድተዋል።

በመሆኑም አካባቢው ከአዋሽ፣ ከቆቃ እንዲሁም ከደምበል ሐይቆች በሚያገኘው ከፍተኛ የመስኖ ውሃ


በዞኑ ከ200 ሺህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

# የኢትዮ-ጅቡቲ ሁለትዮሽ ግንኙነት እየተጠናከረ ይገኛል

- ሁለቱ ሀገራት የኤሌክትሪክ ሽያጭ ስምምነት ተፈራርመዋል

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በርካታ ዓለም አቀፋዊና ቀጠናዊ ተግዳሮቶች ቢኖሩም ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረው የኢትዮጵያና ጅቡቲ የሁለትዮሽ ግንኙነት ከምንጊዜውም


የኢትዮ-ጅቡቲ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# አሸባሪው ትሕነግ ትጥቅ ካልፈታ ከጦርነት አዙሪት ሊወጣ አይችልም


ገጽ 4


# እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናና ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ከተማ መሆኗን የሚያረጋግጡ ናቸው

## - የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲናና በዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ከተማ መሆኗን የሚያረጋግጡና ምቹ ከተማ መሆኗን የሚያሳዩ መሆናቸው ተገለጸ፡፡ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች በከተማ አስተዳደሩ እየተገነቡ ያሉ ሜጋ ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ሂደታቸው እየተፋጠነ የሚገኙ ሜጋ ፕሮጀክቶች ያሉበትን ሁኔታ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ለተውጣጡ ባለሙያዎች ትናንት አስጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት የከተማ አስተዳደሩ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ጠይባ ሎና እንደገለጹት፣ እየተገነቡ ያሉ፣ ግንባታቸው የተጠናቀቁና በግንባታ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች


እየተገነቡ ያሉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡ በገበዘ ገብሬ








500 ለሚጠጉ የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ወጣቶች የማነቃቂያ ሥልጠና ተሰጠ




ገጽ 3

# በክልሉ ከመኸር እርሻ ከ143 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በመኸር ወቅት ከለማው 4 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከ143 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት እንደሚሰበሰብ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለፁ።

ርዕሰ መስተዳድሩ ዶክተር ይልቃል ከፋለ በኩታ ገጠም የለማ የጤፍ ሰብልን በጎበኙበት ወቅት እንዳሉት፤ የመኸሩ ሰብል በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። በተለይም ስንዴ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ አኩሪ አተርና ሌሎች 12 የሰብል አይነቶችን በኩታ ገጠም ማልማት ተችሏል። በዚህም ክልሉ በመኸር ወቅት ከለማው 4 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ከ143 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል፡፡



ምርታማነትን ለማሳደግም አርሶ አደሩ አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን እንዲተገብር የተጠናከረ የባለሙያና የአመራር ድጋፍ መሰጠቱም ርዕስ መስተዳድሩ አስታውሰዋል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ኃይለማርያም ከፍያለው በበኩላቸው “በክልሉ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሰፊ ሥራ ተሠርቷል” ብለዋል።

“አርሶ አደሩ የግብርና ቴክኖሎጂን እንዲጠቀም ከማድረግ ባለፈ በቂ ግብዓት እንዲቀርብ በመደረጉ የመኸር ሰብል ቁመና የታሰበውን ምርት ማግኘት በሚያስችል ደረጃ ላይ ይገኛል” ብለዋል።

በመኸር ወቅቱ የተለያዩ ሰብሎችን በ1 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ በኩታ ገጠም ማልማት የተቻለ ሲሆን ይህም ምርታማነትን ለማሳደግ የጎላ ሚና አለው።

በኩታ ገጠም ከለማው መሬት ከ64 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅም ኃላፊው አስታውቀዋል። በርዕሰ መስተዳድሩ የተመራ የከፍተኛ አመራር ቡድን ትናንት በምስራቅ ጎጃም ዞን ሸበል በረንታ ወረዳ በኩታ ገጠም የለማ የጤፍ ሰብልን ጎብኝቷል።



ፎቶ፡ በሃዱሽ አብርሃ

ኢንጂነር ሃብታሙ ኢተፋ

# የንፁሕ መጠጥ ውሃ ሽፋንን 69 በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋንን 69 በመቶ ለማድረስ እየተሠራ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ሃብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሀገራዊ ሽፋንን አሁን ካለበት 62 ነጥብ 47 በመቶ ወደ 69 በመቶ ለማድረስ እየተሠራ ነው፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ 2014 በጀት ዓመት በበርካታ አካባቢዎች ብዙ የንፁሕ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች በጦርነቱ ምክንያት መንቀሳቀስ ሳይችሉ የቆዩበት ዓመት ነው፡፡ በተለይ የሰሜኑ ጦርነት መኖር የፕሮጀክቶች አለመቀጠል ብቻ ሳይሆን በማስፈፀም አቅም ደረጃ እንዲቀንስ እና የገንዘብ እጥረትም እንዲከሰት አድርጓል፡፡ ስለዚህ ፕሮጀክቶች በታሰበላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ ፈታኝ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ሆኖ ነበር ብለዋል፡፡

ሆኖም በጀት ዓመቱ እነዚህ ችግሮች ለመቋቋም በተደረገው ጥረት ሚኒስቴሩ የሚሠራቸው እና ከክልሎች ጋር በጋራ በሚያከናውናቸው ፕሮጀክቶች ላይ ስኬታማ ሥራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል፡፡

ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ሽፋን በ2012 ዓ.ም ከ55 ነጥብ 7 ያልዘለለ ሽፋን እንደነበረው ያነሱት ሚኒስትሩ በ2013 ደግሞ ይህ የውሃ ሽፋን ወደ 58 ከፍ ብሎ እንደነበር ተናግረዋል፡፡

ይህንን የሽፋን መጠን በ2014 በጀት ዓመት ወደ 62 ነጥብ 47 ማድረስ እንደተቻለ በመግለጽ በ2015 በጀት ዓመት ይህን ቁጥር 69 በመቶ ለማድረስ ይሠራል ብለዋል፡፡


በ2014 በጀት ዓመት በሀገር አቀፍ ደረጃ የመጠጥ ውሃ ሽፋን 62 ነጥብ 47 ለማድረስ የተቻለው በግጭቱ ውስጥ ያሉ አካባቢዎች ጭምር ተደምረው የመጣ ውጤት መሆኑን ያስገነዘቡት ሚኒስትሩ፤ 62 ነጥብ 47 ደርሷል የሚባለው የውሃ ሽፋን የተመረተው የውሃ መጠንና የነዋሪው ሕዝብ መጠን በማስላት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በውሃው ዘርፍ መንገድ ላይ ብክነቶች እና ሕገ ወጥ የውሃ አጠቃቀሞችና አያያዞች መኖራቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ሆኖም እነዚህ ተግዳሮቶች ባሉበት ሁኔታ በገጠር አካባቢዎች በሰው ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት በታች በሆነ ቦታ ውስጥ በአንድ ቀን 25 ሊትር ማግኘት እንዲቻል ሁኔታዎች ተመቻቸተዋል ብለዋል፡፡

በከተማ ደረጃ ደግሞ እንደየከተሞቹ ሁኔታ ከ40 እስከ 100 ሊትር በአንድ ቀን ለአንድ ሰው ከአንድ ኪሎ ሜትር ርቀት በታች ማዳረስ ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አሁን በሀገሪቱ ያለው የውሃ ሽፋን ለኢትዮጵያ እንደ ታዳጊ ሀገር ተገቢ ደረጃ ላይ መድረሷን የሚያመላክት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ ማለት ግን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ ሊሆን ችሏል ማለት አይደለም ብለዋል፡፡

የውሃ ምርት ከሕዝብ ቁጥር ጋር በንፅፅር የሚሠራው በአማካይ ስለሆነ በአንዳንድ አካባቢዎች ያለው መጠን ከሌሎች ሊለይ የሚችልበት አጋጣሚ እንደሚኖርም አክለው ገልጸዋል፡፡



# በክልሉ በ2015፡- - ከ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የምገባ ተጠቃሚ ሆኑ - የ22 ሺህ አረጋውያንና አቅመ ደካሞች ቤት ታድሷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-በኦሮሚያ ክልል በ2015 ከ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ተገለጸ። በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የ22 ሺህ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ እናቶች ቤት ማደስ መቻሉም ተጠቁሟል።

በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የኦሮሚያ ክልል የማኅበራዊ ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱልሐኪም ሙሉ እንደገለጹት፤ በኦሮሚያ ክልል የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ምገባ ተጀምሯል። በዚህም በኦሮሚያ ክልል ከ7 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ምገባ ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በተመሳሳይ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 6 ሺህ 400 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ግንባታ በሕዝብ ተሳትፎ መጀመራቸውን ገልፀው፤ ከዚህ ውስጥ 2 ሺህ 441 የሚሆኑት መጠናቀቃቸውን ተናግረዋል።

በቅርቡ በክልሉ 300 ሺህ የሚጠጉ ተማሪዎች የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና መውሰዳቸውን ያስታወሱት አቶ አብዱልሐኪም፤ ለተማሪዎች በቂ ትራንስፖርት በመመደብና ተገቢውን ወጪ በመሸፈን ወደሚፈተኑበት ዩኒቨርሲቲ ማድረስ መቻሉም ትልቅ ስኬት ነበር ብለዋል።

በዚህም ለትምህርት ጥራት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይነትም የተሻለ ተግባራት ለማከናወን አቅጣጫ ተቀምጧል ነው ያሉት።

በተመሳሳይም በኦሮሚያ ክልል ባለፉት ሶስት ወራት በተከናወነ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት 22 ሺህ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ ቤቶች ማደስ መቻሉ ተናግረዋል። በሩብ ዓመቱ በበጎ ፈቃድ ወይም በዜግነት አገልግሎት የሕዝቡን ኑሮ የሚያሻሽሉ ሥራዎች ተሠርተዋል። በማኅበራዊ ክላስተር በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በትምህርት፣ በጤናና የዋጋ ንረትን በማረጋጋት ረገድ የተሻለ ሥራ መሠራቱን አንስተዋል።

በዚህም በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 22 ሺህ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ እናቶች ቤት ማደስ ተችሏል ያሉት አቶ አብዱልሐኪም፤ በዚህም ከክልሉ ጀምሮ በየደረጃው ያሉ የወጣቶችና ሴቶች አደረጃጀት ተሳትፈውበታል ብለዋል።

በተጨማሪ የክልሉ ባለሃብቶች፣ ተቋማትና ድርጅቶች ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ የተወጡበት ወቅት ነበር ነው ያሉት።

በጤና ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ለማስጠበቅ፣ የመድኃኒት አቅርቦትና ስርጭት ማነቆዎችን ለመቅረፍ የሕዝብ መድኃኒት ቤቶችና ሞዴል መድኃኒት ቤቶችን የማደራጀት ሥራ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት መሠራቱንም ተናግረዋል።

በመደበኛ ፍርድ ቤቶች ያሉትን የሥራ ጫናዎች ለመቀነስና ፈጣን የፍትሕ አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ ባህላዊ ፍርድ ቤቶችን እስከ ቀበሌ ድረስ የማደራጀት ሥራ ውጤታማ እየሆነ መምጣቱንም አስታውሰዋል።

በተመሳሳይ የኦሮሞን ሕዝብ የመረዳዳት ባህል ተቋማዊ ለማድረግ ‘ቡሳ ጎኖፋ’ ተቋም እስከ ወረዳ ድረስ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ማደራጀት እንደተቻለም ተናግረዋል።

አቶ አብዱልሐኪም በክልሉ ሌብነትና የጥቅም ጥገኝነትና ጠንካራ ተጠያቂነት ያለመኖር ቁልፍ ችግሮች መሆናቸውን ገልጸው፤ ችግሮቹን ለመቅረፍም የአገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ በመምራት ‘ዲጂታላይዜሽን’ ማድረግ ላይ በትኩረት እንዲሚሠራ ጠቁመዋል። በተጨማሪም ሕዝቡ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የድርሻውን መወጣት አለበት ማለታቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# 500 ለሚጠጉ የበጎ ፈቃድ አገልጋይ ወጣቶች የማነቃቂያ ሥልጠና ተሰጠ



ፎቶ፡ በአዮብ ተፈራ



**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር በመልካም ስብዕና ግንባታ፤ በበጎ አድራጎት አስተሳሰብና ተግባር ላይ ለ478 የአዲስ አበባ ወጣቶች ያዘጋጀው የማነቃቂያ ሥልጠና በትናንትናው ዕለት ተሰጥቷል።

በሥልጠናው መክፈቻ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰ፣ "በሥልጠናው ላይ የተገኙ ወጣቶችን እናንተ ቀና ልብ ኖሯችሁ በማገልገል ተግባር ውስጥ ስለገባችሁ ስለኢትዮጵያ ቁርጠኛነታችሁን በተግባር አሳይታችኋል" ሲሉ የወጣቶችን የበጎ ፈቃድ ተግባር በመጥቀስ አመስግነዋል።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ወራሪ ጠላቶቿን እንጂ ድህነቷን ሙሉ በሙሉ አላሸነፈችም ያሉት አቶ ጌትነት፤ ድህነቷን በመርታት አሸናፊ ሆና ልትወጣ የምትችለው በወጣቶቿ የተባበረ ክንድ ነው። ይህ ትውልድ ደግሞ የዳግም አድዋ ትውልድ በመሆኑ ሀገሩን ወደ አሸናፊነት ከፍ ያደርጋል ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደ ተቋም ትልልቅ ሀገራዊ ኃላፊነቶችን እየተወጣ መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ስለ ኢትዮጵያ በሚባለው መድረኩ ኢትዮጵያ እያሸነፈች የምትሻገር ሀገር መሆኗን፣ መነጋገር እና መግባባት የምንችል ሕዝቦች መሆናችንን በ12 ከተሞች በማካሄድ አሳይቷል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የኢትዮጵያ የዕድገት መሠረቶች ወጣቶች መሆናቸውን ጠቁመው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ለነገ ሀገር ተረካቢ ባለ ቅን ልብ ወጣቶች የማነቃቂያ ሥልጠና ማዘጋጀቱን ወደፊትም እንደሚቀጥል አብራርተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አብርሃም ታደሰ በበኩላቸው፣ በከተማዋ ከ1 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች በበጎ ፈቃድ ሥራ ላይ ተሠማርተው መቆየታቸውን ጠቁመው አዲስ አበባ የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች ከተማ ሆናለች ብለዋል።

በተለያዩ ዘርፎች የወጣቶች ተሳትፎ አይተኬ መሆኑን አቶ አብርሃም ጠቅሰው፤ ካለ ወጣቶች ተሳትፎ የምትገነባ ሀገር የትም ልትደርስ ስለማትችል ወጣቶች የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ተሳትፏቸው ሊያድግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የማነቃቂያ ሥልጠናው የበጎ ፈቃድ ተግባራቸውን በመልካም ሥነ ምግባር ታጅበው እንዲያከናውኑ የሚያግዝ መሆኑን አብራርተዋል።

የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና በበኩላቸው፣ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት በጎ ፈቃድ ሥራው ከሚያስገኘው ጥቅም ባሻገር የሚተጋገዝ፣ የሚረዳዳና ባለ መልካም ስብዕና ትውልድ ለመገንባት የሚጠቅም መሆኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት በተለይም በአዲስ አበባ በበጎ ፈቃድና በሌሎች ዐውዶች ያለው የወጣቶች ተሳትፎ የሚደነቅ መሆኑን ያነሱት ፕሬዚዳንቱ፤ የአዲስ አበባ ወጣቶች የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት ምሣሌዎች ናችሁ ሲሉ አሞግሰዋል።

መሰል የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ወጣቶችን የሚያበረታቱ እና የሚያነቃቁ መድረኮች መቀጠል ይኖርባቸዋል፤ ኮተቤ የትምህርት ዩኒቨርሲቲም ድጋፍ ማድረጉን ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከመደበኛ ሥራው ጎን ለጎን ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ሥልጠናውን ያዘጋጀ ሲሆን፤ የሥልጠናው ዓላማ የበጎ አድራጎት ሥራ በቅስቀሳ እና በተለያዩ መንገዶች የሚከናወን ሳይሆን ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት ወደ በጎ አድራጎት ሥራ እንዲሠማሩ ማስቻል ነው ተብሏል።

የአዲስ አበባ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ፣ የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሰቲ እና ኮካኮላ ቤቬሬጅስ አፍሪካ ኢትዮጵያ ከኢፕድ ጋር በመተባበር ሥልጠናውን እንዲሳካ አድርገዋል።

# ኢትዮ ቴሌኮም የቴሌ ክላውድ አገልግሎትን በይፋ አስጀመረ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የደንበኞቹን የቢዝነስ ሥራዎች ለማዘመን የሚረዳውን የቴሌ ክላውድ (Tele cloud-IaaS, PaaS & SaaS) አገልግሎት ትናንትና በሳይንስ ሙዚየም በይፋ አስጀመረ። የኢትዮ ቴሌኮም የክላውድ አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ ከመሆኑ ባሻገር የተቋማትን ወጪና ጊዜ በመቆጠብ ረገድ ተመራጭ መሆኑን ኢትዮ ቴሌኮም አስታውቋል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ እንደገለጹት፤ የቴሌ ክላውድ አገልግሎትን በመጠቀም ተቋማት ለቴክኖሎጂ መረጣ፤ ለመሠረተ ልማት ግንባታ፣ ስልጠናና ጥገና የሚወስደውን ጊዜ እንዲሁም የውጪ ምንዛሪ ክፍያ ማስቀረት ይችላሉ።

ተቋማት የቢዝነስ እንቅስቃሴያቸውና የአገልግሎት ጥራታቸውን በማሳደግ ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ በማድረግ ተወዳዳሪነትና ምርታማነት እንዲጨምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብለዋል።

በተጨማሪ ቴሌ ክላውድ አገልግሎት ፍላጎትን ተከትሎ ሊስፋፋ የሚችል የሃብት አጠቃቀም ተግባራዊ የሆነበት ሥርዓት በመሆኑ ተቋማት እንደየአገልግሎታቸው ስፋትና መጠን አሠራራቸውን እያሳደጉ እንዲሄዱ ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

ፍሬሕይወት ታምሩ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮ ቴሌኮም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የግልና የመንግሥት ተቋማት ከፍተኛ የመረጃ ክምችትና አጠቃቀም እንዲሁም ተዛማጅ የዳታ ማዕከል አገልግሎት ፍላጎት መሠረት አድርጎ ቴሌ ክላውድን አስጀምሯል።

የቴሌ የክላውድ አገልግሎቶቹን በሦስት አማራጭ ያቀረበ መሆኑን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ሦስቱንም አማራጮች መጠቀም የሚቻልበት አሠራር እንዳለ ጠቁመዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ በቴክኖሎጂው አማካኝነት ተቋማት የራሳቸው የመረጃ ማዕከል መገንባት ሳያስፈልጋቸው ካሉበት ሆነው ደህንነታቸው በተጠበቁ የመረጃ ማዕከላት መረጃዎቻቸውን ማከማቸት፣ መቀመር ብሎም የእራሳቸውን አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ገልጸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሶፍትዌር አልሚዎች ካሉበት ሆነው ላበለፀጓቸው ሶፍትዌሮች የተሟላ የዳታቤዝ ማኔጅመንት ሲስተም መጠቀም እንደሚያስችላቸው ጠቁመዋል።



ፍሬሕይወት ታምሩ

በሶስተኛ ደረጃ ደንበኞች የተለያዩ በውጭ ምንዛሪ ክፍያ በመክፈል ያገኟቸው የነበሩ ሶፍትዌሮችን ከቴሌ ክላውድ በተመጣጣኝ ክፍያ በብር በማግኘት መጠቀም እንደሚችሉ አስረድተዋል።

በተለይም ደንበኞች በቢሯቸው የጽሑፍና ሌሎች የቢሮ አገልግሎቶች የሚያከናውኑበት የኦፊስ መተግበሪያ መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ለቪዲዮ ምስሎቻቸው ማስተዳደሪያና ዳታ ቋት አገልግሎትም ያገኛሉ። በሌላ በኩል የርቀት ትምህርት በዘመናዊ መልኩ ለማቅረብ የሚረዳ አገልግሎትንም መያዙንም ገልጸዋል።

ቴሌ ክላውድ ለ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ፤ አስፈላጊው የቴክኒክ ድጋፍ ሲያስፈልግም ብቁ ባለሙያዎች ደንበኞችን ለማገልገል ዝግጁ ሆነው እንደሚጠብቁ ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የሦስት ዓመት መሪ የዕድገት ስትራቴጂው አዘጋጅቶ የደንበኞቹን የዕለት ተዕለት የቢዝነስ እንቅስቃሴ ለማዘመን መወጠኑን ያስታወሱት ፍሬሕይወት ታምሩ፤ የቴሌ ክላውድ አገልግሎትም የዚሁ ዕቅድ አካል እንደሆነ ጠቁመዋል።

ቴሌ ክላውድን መጠቀም የሚሹ ደንበኞቻችን cloud.ethiotelecom.et ድረ ገጽን ተጠቅመው አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችሉና ክፍያቸውንም በቴሌብር አማካኝነት መፈጸም እንደሚችሉ ኢትዮ ቴሌኮም አስታውቋል።

# ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ አውደ ርዕዮችና ጉባኤዎች መዳረሻ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ ዐውደ ርዕዮችና ጉባኤዎች መዳረሻ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን የኢፌዴሪ ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ:: ከጥቅምት 17 እስከ 19 ቀን 2015 ዓ.ም የሚቆይ 11ኛው የዶሮ ኤክስፖና ሰባተኛው የእንስሳት ሀብት ዐውደ ርዕይና ጉባኤ በአዲስ አበባ ከተማ ተከፍቷል::

በዐውደ ርዕዩ መክፈቻ ላይ የተገኙት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የቱሪዝም የግብይትና ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት እንደገለጹት፤ ሚኒስቴሩ በኢትዮጵያ ኮንቬንሽን ቢሮ አማካኝነት እና ሀገር አቀፍ ዐውደ ርዕዮች እና ጉባኤዎች መዳረሻ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ::

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፤ ሰባተኛው የእንስሳት ሀብት ዐውደ ርዕይና 11ኛው የዶሮ ኤክስፖ በዶሮ ተዋፅዖ ምርት እና ተያያዥ ዘርፎች የገበያ ትስስርን፣ የቴክኖሎጂ ትውውቅን እና የዕውቀት ሽግግርን በማዘመን ደረጃ ጉልህ አስተዋፅዖ አለው::

ዐውደ ርዕዮች እና ጉባኤዎች ለዘመናት ለትውልድ የፈጠራ ችሎታ መድረክ፣ ለንግድ ማኅበረሰብ የትስስር መናኸሪያ እና የቴክኖሎጂ ውጤቶች ማስተዋወቂያ መድረክ በመሆን አገልግለዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ከመቼውም ጊዜ በላይ ለኢኮኖሚ እና ለማኅበራዊ ዘርፎች መስፋፋት እና ልማት የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ በጎላበት ዘመን እንገኛለንም ነው ያሉት::

በርካታ ኮንፈረንሶች፣ የንግድ ባዛሮች እና ዐውደ ርዕዮች በመስተናገድ ላይ እንደሚገኙ ያመላከቱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ኢትዮ ፖሊቴሪ ኤክስፖም ሀገራችንንም ሆነ ከተማችንን የበለጠ ለማስተዋወቅ በተለያዩ ዘርፎች ያሉንን እምቅ ሀብቶችን ከዓለም አቀፉ የንግድ ማኅበረሰብ ጋር ለማስተሳሰር እና የቴክኖሎጂን ሽግግር ለማሳለጥ ጉልህ ሚና እንዳለው ይታመናል ብለዋል::

ሁነቱን የሚያስተባብረው የፕራና ኢቨንትስ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ነብዩ ለማ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በዐውደ ርዕዩ ላይ ከ10 ሀገራት ማለትም ከኢትዮጵያ፣ ከፈረንሳይ፣ ከጀርመን፣ ከሃንጋሪ፣ ከሕንድ፣ ከኬንያ፣ ከኔዘርላንድ፣ ከስኮትላንድ፣ ከቱርክ እና ከአሜሪካ የተውጣጡ ከ70 በላይ ኩባንያዎች ተሳታፊ ናቸው::



**ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት**

በኤክስፖው የዶሮና ወተት እሴት ሰንሰለትን ለመለወጥ ከፍተኛ የፖሊሲ ውይይት እና ስልጠና ይሰጣል፤ ያሉት አቶ ነብዩ፤ ኤክስፖው የግብርናን ምርታማነት በማሻሻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆኑንም ጠቁመዋል።

11ኛው የዶሮ ኤክስፖ እና 7ኛው የእንስሳት ሀብት ዐውደ ርዕይ በወተት፣ በዶሮ እና የሥጋ እሴት ትስስር በመፍጠር፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በማስተዋወቅ፣ የእውቀት ሽግግርን በማምጣት የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ያስተዋውቃልም ነው የተባለው::

ይህ የንግድ ትርኢት በመንግሥት በኩል በግብርና ሚኒስቴር በኩል የሚደገፍ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ የኔዘርላንድስ የልማት ድርጅት፣ የኢትዮጵያ እንስሳት ልማት ማኅበር፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ዶሮ አርቢዎችና አቀነባባሪዎች ማኅበር የሁነቱ የሀገር ውስጥ አጋር መሆናቸውም ተመላክቷል::

ፕራና ኢቨንትስ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘርፈ ብዙ የንግድ ትርዒት እና የቢዝነስ ኩነቶች በማዘጋጀት እና በማማከር ሥራ ላይ የተሠማራ እና ዘርፉን በእውቀት በቴክኖሎጂ እና በግብዓቶች ለመደገፍ ዓላማ አድርጎ የተቋቋመ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ነው::

ዜና



አቶ ኃይለ ገብረሚካኤል

# አሸባሪው ትሕነግ ትጥቅ ካልፈታ ከጦርነት አዙሪት ሊወጣ አይችልም

መኣርግ ገ/ሄር

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ትሕነግ ትጥቅ ካልፈታ በስተቀር በሰላማዊ መንገድ ወደ ሰላም ሊመለስ የሚችል ቡድን አለመሆኑን የብልጽግና ፓርቲ የትግራይ ቅርንጫፍ አመራር ገለጹ፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት የክትትልና ቁጥጥር ምክር ቤት ኃላፊና የብልፅግና ትግራይ ቅርንጫፍ አመራር አቶ ኃይለ ገብረሚካኤል በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ አሸባሪው ትሕነግ ሰላም የማይገባውና ሁል ጊዜ በጦርነት መኖር የሚፈልግ የጥፋት ቡድን ነው፡፡

ቡድኑ ከሰላም ይልቅ በጦር አፈሙዝ የሚያምን በመሆኑ ይህንን የሚተማመንበትን የጦር አፈሙዝ ከእጁ ካልተነጠቀ ሰላም አይሰጥም ያሉት አቶ ኃይለ፣ ቡድኑ በተደጋጋሚ ጦርነት መክፈቱም ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ኃይለ እንደተናገሩት፤ በትግራይ ክልል ሰላም እንዲሰፍን ከተፈለገ አሸባሪው ትህነግ ትጥቁን ፈቶ ለፈጸመው ወንጀል ይቅርታ ሊጠይቅ ይገባል፤ ለሠራው ወንጀልም ተጠያቂ መሆን አለበት፡፡ አለበለዚያ ግን ሰላም ሊሰጥ አይችልም፡፡

እንደ አቶ ኃይለ ገለጻ፣ አሸባሪው ትሕነግ እንደ መንግሥት መሣሪያ ይዞ ለሰላም ንግግር መቀመጥ የለበትም፤ ምክንያቱም ወንጀል የፈፀመ ቡድን እንጂ መንግሥት አይደለም።

በተለይ በትግራይ ሕዝብ ከባድ ወንጀል ፈጽሟል። በዚህም ብዙ ንብረት እና የሰው ሕይወት ጠፍቷል። በመሆኑም ቡድኑ በዘር ማጥፋት ወንጀልም ተጠያቂ ሊሆን ይገባዋል፡፡

በሌላ በኩል መንግሥት በትግራይ የሚገኙ የመሠረተ ልማቶችን መልሶ ወደመጠገን መግባቱ ለትግራይ ሕዝብ ትልቅ ተስፋ ነው፤ሕዝቡ ሰላም፣ ልማት፣ ዴሞክራሲና ፍትሕ እንዲሰፍን ያግዛል ሲሉ ተናግረዋል።

አሸባሪው ትሕነግ የትግራይ ሕዝብ ችግር ብቻ ሳይሆን የመላዋ ኢትዮጵያ ስጋት ነው ያሉት አቶ ኃይለ፤ በመሆኑም ይህ ቡድን ተጨማሪ ጥፋት እንዳይፈጽም ትጥቅ መፍታት አለበት ብለዋል፡፡

የትሕነግ አሸባሪ ቡድን እጁ ረጅም ነው፤ በአማራ እና አፋር ክልል ሳይቀር ወንጀል ፈጽሟል። የሕዝቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በማስተጓጎል የበርካታ ሰዎች ሕይወትና ንብረት እንዲጠፋ አድርጓል፤ በመሆኑም ይህ ቡድን ከዚህ በላይ ጥፋት እንዲፈጽም እድል ሊሰጠው አይገባም፡፡

የትግራይ ሕዝብ ከአሸባሪው ሕወሓት ሙሉ በሙሉ ከተላቀቀ ሕዝቡ ከሥቃይና ከመከራ ነፃ ሆኗል ማለት ነው ሲሉም ጠቁመዋል።

መንግሥት የጦርነትን ውጤት በመረዳት ጦርነቱን ለማስቀረት ብዙ ጥረት አድርጎ ነበር፤ ነገር ግን በአሸባሪው ቡድን በኩል ተመሳሳይ ፍላጎት ባለመኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የትግራይ ሕዝብ ከፍተኛ ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ምክንያት ሆኗል ሲሉም ተናግሯል።

# ትኩረቱን ሥራ ፈጠራ እና ሙያ ልማት ላይ ያደረገ ማኅበር ተመሠረተ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ባለሙያዎችና የኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት ሙያን እንዲያለሙ፣ እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲያሻሽሉ፣ ግብዓቶችን እንዲያገኙና የሰው ኃይል ልማትን እንዲያዘምኑ የማስቻል ዓላማን የሰነቀው "አሶሴሽን ፎር ታለንትድ ዴቨሎፐመንት ኢን ኢትዮጵያ" (ATD) የተሰኘ ማኅበር ተመሠረተ።

በምሥረታ መርሐ ግብሩ የተገኙት የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን፤ ኢትዮጵያ ከዘርፈ ብዙ ችግሮቿ እንድትላቀቅ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች እንደሚያስፈልጋትና እንደታለንት ዴቨሎፐመንት ዓይነት ማኅበራትን በመፍጠር ሙያን አዳብሮ ወደ ሥራ መለወጥ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሥራ ዕድል ፈጠራ የግለሰቦችና የማኅበራት ሚና ከፍተኛ እንደመሆኑ መንግሥት ከታለንትድ ዴቨሎፐመንት ማኅበር ጋር በመቀራረብና በመደጋገፍ እንደሚሠራም ነው የገለጹት።

ማኅበሩ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያንን በማስተባበርና በሀገር ውስጥ በተለያዩ ሙያዎች ላይ የሚገኙ በጎ ፍቃደኞችን በማሰባሰብ ውጤታማ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባም ነው አቶ ንጉሱ ያሳሰቡት።

ከሀገር በቀል ሪፎርም ጋር የተጣመሩት የአስርና የአምስት ዓመት የሥራ ዕድል የድርጊት መርሐ ግብርና ስትራቴጂክ እቅዶችን ለማሳካት ሚኒስቴሩ ክህሎቱ የዳበረ፣ ገበያው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ማምረት ላይ ማተኮሩንም ጠቁመዋል።

የሚፈጠረው የሥራ ዕድል እና የሥራ ፈላጊው ቁጥር ባለመጣጣሙ የሥራ አጥነት ምጣኔው ከፍተኛ መሆኑን፣ ችግሩን ለመቅረፍ በ2030 እአአ 20 ሚሊዮን አዳዲስ የሥራ ዕድሎች ለመፍጠር ትኩረት መሰጠቱን አመልክተዋል።

እቅዱን ለማሳካትም በየዓመቱ ሦስት ሚሊዮን ሥራዎችን ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑንና ዘንድሮ ሦስት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ቋሚ የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

ወጣቶች በተለይም ሴቶች ከቅጥርና ከጠባቂነት ተላቅቀው የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩ፣ ተደራጅተው ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ የፋይናንስ፣ የመሠረተ ልማት፣ የመሥሪያና የመሸጫ ቦታና የገበያ ትስስር እንዲያገኙ መንግሥት ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

የማኅበሩ የቦርድ ሊቀመንበር ዶክተር ገመቹ ዋቅቶላ በበኩላቸው፤ በአሁኑ ወቅት ታለንት የዓለም አቀፍ አጀንዳ መሆኑን፣ በኢኮኖሚ ዕድገት በጎ ተጽዕኖ እንዳለው፣ ተሰጥዖን ለመለየትና ለማሳደግም ትልቅ ፈተና መሆኑንም ጠቁመዋል። ዘርፉን በመደገፍ ውጤታማ ለማድረግ ማኅበሩ ትኩረት እንደሚሰጥም ገልጸዋል።



አቶ ንጉሱ ጥላሁን

ውጤታማና ተወዳዳሪ መሆን የሚቻለው ሰፊ ቴክኖሎጂዎችን የሚፈጥር፣ አሠራሮችን የሚያዘምን እና መጪውን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ መምራት የሚችል የሰው ኃይል ማልማት ሲቻል ነው ያሉት ዶክተር ገመቹ፤ ማኅበሩ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመደገፍ የሚያስችል እቅድ መንደፉን ነው የገለጹት።

በኢትዮጵያ የተለያዩ የሰው ሃብት ልማት ተግባራት ቢኖሩም አብዛኞቹ በመንግሥት በግለሰቦችና በልማት አጋሮች ጥረት የሚከናወኑ ናቸው። ጥረቶቹን ማገዝና ብቁና ተወዳዳሪ ከማድረግ አንጻር በዘርፉ ያሉ ፕሮፌሽናሎች በተደራጀ መልኩ ሚናቸውን እንዲወጡ ማድረግ ይገባልም ብለዋል። ማኅበሩ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ተመዝግቦ የተቋቋመ ለትርፍ የማይንቀሳቀስ ድርጅት መሆኑንም ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ከበለጸጉ ሀገራት ጋር ስትወዳደር በሰው ሃብት ተሰጥዖ ልማት ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅባት፣ ሀገራዊ ሃብትንም በመጠቀም ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር እንደሚያስፈልግም ነው ያሳሰቡት።

ተሰጥዖን የማልማት ሥራ ለመንግሥት ወይንም ለተወሰኑ ድርጅቶች የሚተው ሳይሆን፤ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ጠንካራ ተሳትፎ ይፈልጋልም ነው ዶክተር ገመቹ ያሉት።

በ2019 በዓለም የኢኮኖሚ ፎረም በተደረገና 141 ሀገሮችን ግምት ውስጥ ያስገባ ጥናት በእውቀት 137ኛ ደረጃ ላይ መቀመጧን፣ በተመራቂዎች ብዛት 128ኛ እንዲሁም በሰው ኃይል ልማት 115ኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ ጥናቱን ጠቅሰው አመልክተዋል።

## እየተገነቡ ያሉ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ጉብኝት ዋና ዓላማው ያሉ ፕሮጀክቶችን ኅብረተሰቡ እንዲያውቅና በባለቤትነት ስሜት እንዲይዝ ለማድረግ ነው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር አያልነሽ ሀብተማሪያም እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደሩ በርካታ ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜ እየተገነቡ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በከተማ መስፋፋት ምክንያት የልማት ተነሽ የሆኑ ከ2 ሺ በላይ የሚሆኑ አርሶ አደሮችን ከእነ ቤተሰቦቻቸው ተጠቃሚ የሚያደርግ የልማት ተነሽ አርሶ አደሮች የእንስሳት እርባታና ተዋፅዖ ማዕከል አንዱ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በ14 ሺ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ሲሆን ሦስት መቶ ከብቶችን የሚያደልብ፣ ሦስት መቶ የወተት ላሞችን የሚይዝ፣ እያንዳንዳቸው 10 ብሎኮች ያሉት ነው፡፡ በተጨማሪም 40ሺ ዶሮዎችን በማርባት በቀን 30 ሺ እንቁላል ያስገኛሉ፡፡ ይህም ለከተማ አስተዳደሩ ማኅበረሰብ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ግንባታውም 88 በመቶ ተጠናቋል ብለዋል፡፡

ኢንጂነር አያልነሽ፤ ግንባታቸው እየተፋጠኑ ካሉት ፕሮጀክቶች መካከል የትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል አንዱ ሲሆን ማዕከሉ አዲስ አበባ አፍሪካ መዲናና የበርካታ ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ መቀመጫነቷን የሚመጥን የትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል እየተገነባ ነው፡፡ ግንባታው 90 በመቶው ተጠናቋል ነው ያሉት፡፡

የአዲስ አበባ የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ደቦ ቶንካ የግራንድ የመኪና ማቆሚያውን ባስጐበኙበት ወቅት እንደገለጹት፣ የሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመ በሦስት ዓመት ውስጥ የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክትን ጨምሮ ሦስት ፕሮጀክቶችን አጠናቆ አስመርቋል። የግራንድ መኪና ማቆሚያው አራተኛው ነው። ፕሮጀክቶቹ አዲስ አበባን በአዲስ መንገድ የማነጽ አካል ናቸው።

ኢንጂነሩ እንዳሉት፣ የግራንድ መኪና ማቆሚያው በአንድ ጊዜ አንድ ሺህ መኪኖችን ማስተናገድ የሚችል ሲሆን ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን ያሟላ ነው፡፡ ግንባታው መቶ በመቶ መጠናቀቁን ገልጸው በቅርቡ ተመርቆ ወደ ሥራ ይገባል፡፡ የመኪና ማቆሚያው በ9 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈና 1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ወጪ የተደረገበት ፕሮጀክት ነው።

ባለ 4 ደረጃዎች ቤዝመንት ያለው ሲሆን አንድነት ፓርክንና የሳይንስ ሙዚየምን ያስተሳሰረ ዘመናዊ ግንባታ ነው፡፡ ግንባታውን ለማጠናቀቅ ሦስት ዓመታት የፈጀ ሲሆን የከተማዋን የሜጋ ፕሮጀክቶች የመፈፀም አቅም ማሳያ መሆኑን ኢንጂነሩ ተናግረዋል።

ፕሮጀክቶቹ ግራንድ የመኪና ማቆሚያ፣ የየካ ቁጥር 2 የመኪና ማቆሚያ፣ የትራፊክ ማኔጅመንት ማዕከል፣ የሕፃናትና ወጣቶች ቴአትር፣ የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ማቋቋሚያ፣ የአቃቂ ቃሊቲ ተገጣጣሚ ቤቶች እና የኮልፌ የገበያ ማዕከል ናቸው፡፡

ፕሮጀክቶቹ አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና እና ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ከተማ መሆኗን የሚያረጋግጡ እና የከተማዋን ገፅታ የሚቀይሩ ናቸውም ተብሏል።

በ2014 በጀት አመት ከ300 በላይ ፕሮጀክቶች ግንባታቸው ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ውለዋል።

## የኢትዮ-ጅቡቲ ሁለትዮሽ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በላይ እየተጠናከረ መሆኑ ተገለጸ። ሁለቱ ሀገራት የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ስምምነት ተፈራርመዋል።

በ16ኛው የኢትዮ-ጅቡቲ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ መዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ እንደተገለጸው፥ ሁለቱ ሀገራት ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረ የሕዝብ ለሕዝብ፣ የፖለቲካ፣ የንግድ፣ የኢኮኖሚ፣ የባሕልና የቋንቋ ግንኙነቶች አሏቸው፤ በአሁኑ ወቅትም እነዚህ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች በርካታ ዓለም አቀፋዊና ቀጠናዊ ተግዳሮቶችን ተቋቁመው ከምንጊዜውም በላይ እየተጠናከሩ ይገኛሉ።

የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኰንን እንደተናገሩት፥ ሁለቱ ሀገራት በብዙ ነገሮች የተሳሰሩ ናቸው።

ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሌሎችም ጥቅሞች ባስጠበቀ መልኩ በሁለቱ ሀገራት መካከል የሚደረጉ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ለቀጠናው ሀገራት ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ እንዳላቸው አቶ ደመቀ አብራርተዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ፥ ስብሰባው በሁለቱ ሀገራት መካከል ስላለው ሁለንተናዊ ግንኙነት ዙሪያ ላይ ያተኮረ ሲሆን በትራንስፖርት፣ በንግድ፣ በፋይናንስ፣ በሎጀስቲክስ፣ በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲና ሌሎችም ዘርፎች ላይ ውይይት ተደርጎባቸዋል።

አክለውም፣ ከዚህ በፊት የተደረጉ ስምምነቶች አፈጻጸምን ማፋጠን በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያም ስምምነት ላይ ተደርሷል ብለዋል።

የጅቡቲ የውጭ ጉዳይና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስትር መሐሙድ አሊ ዩሱፍ በበኩላቸው፥ ዓለም ባለፉት ዓመታት የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ፣ የሩሲያና ዩክሬን ጦርነትና መሰል ፈተናዎችን አስተናግዷል፤ የአፍሪካ ቀንድም የራሷ የሆኑ ተግዳሮቶች ገጥመውት ነበር፤ ነገር ግን ረጅም ዘመናትን ያስቆጠረው የኢትዮጵያና ጅቡቲ የሁለትዮሽ ግንኙነት በእነዚህ ጫናዎች ውስጥ ቢሆንም ከምንጊዜውም በላይ እያደገ መሆኑን አብራርተዋል።

ሁለቱ ሀገራት በንግድ፣ ትራንስፖርት፣ ኢኮኖሚና በሌሎችም ዘርፎች ያሏቸው ግንኙነቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉና እየተጠናከሩ መሆኑንም አስረድተዋል።

"ሰሞኑን ከኢትዮጵያ የልዑካን ቡድን ጋር በመሆን በጅቡቲ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር አስጀምረናል" ያሉት ሚኒስትሩ፤ ትናንት ደግሞ የሁለቱ ሀገራት የኤሌክትሪክ አቅራቢ ድርጅቶች የኤሌክትሪክ ኃይል ሽያጭ ስምምነት ተፈራርመዋል ብለዋል።

እንደሚኒስትሩ ገለጻ፥ በ16ኛው የኢትዮ-ጅቡቲ የሚኒስትሮች የጋራ ኮሚሽን ስብሰባ ወቅት የሁለቱን ሀገራት የሁለትዮሽ ትብብር ለማጠናከር ጥሩ ተሞክሮዎችን መጠቀም በሚቻልባቸው መንገዶች ዙሪያ ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

ሚኒስትሩ የጅቡቲ የልዑካን ቡድን በኢትዮጵያ የነበረውን ቆይታ ሲገልጹ፥ "እንደ ሁልጊዜው በአዲስ አበባ በነበረን ቆይታ ከቤተሰቦቻችን ጋር በቤታችን እንደሆንን ተሰምቶናል፤ ኢትዮጵያውያን እህትና ወንድሞቻችን ላሳዩን ትህትና የተሞላበት የእንግዳ አቀባበል ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል" ሲሉ አመስግነዋል።

## በዞኑ ከ200 ሺህ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ሀብት በዓመት ሦስት ጊዜ በማልማት አርሶ አደሩ ተጠቃሚ እየሆነ ሲሆን በአካባቢው የስንዴ ልማት ላይ በሁለት ዙር እንዲያለማ በማድረግ በሦስተኛው ዙር የአትክልት ምርት እንዲያለማ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለዚህም ከሰባት ሺህ በላይ የውሃ መሳቢያ ሞተር ፓምፖችንና ሌሎች የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን ለአርሶ አደሩ በማከፋፈል እንዲሁም የባለሙያ እገዛዎችን በማከል ውጤታማ እንዲሆን የሚደረግ መሆኑን ዋና አስተዳዳሪው ተናግረዋል።

በበጋ ከሚለማው የመስኖ ስንዴ ልማትም ከአንድ ሚሊዮን ኩንታል በላይ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በባለፈው የክረምት ምርት ከ6 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ እንደሚገኝ የገለፁት አቶ አባቡ፤ ከዚህ ውስጥ ስምንት መቶ ሺህ ኩንታል ምርት ለውጪ ገበያ የሚቀርብ መሆኑን አመልክተዋል።

የምሥራቅ ሸዋ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ መስፍን ተሾመ በበኩላቸው በወረዳው 85 በመቶ የሚሆነው መሬት በኩታ ገጠም እንዲሁም 75 በመቶ በመካናይዝድ እርሻ እንዲያመርት በማድረግ የሚመረተው ምርት በጥራት ፣ ከብክነት የፀዳና የአርሶ አደሩን ጊዜና ጉልበት በቆጠበ መልኩ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የአርሶ አደሩን ምርት ለገበያ ለማቅረብ ከተለያዩ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች ጋር በማስተሳሰር አምራቾች በገበያ እጦት እንዳይቸገሩ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

በቀጣይ የመጀመሪያው ዙር የመስኖ ልማት መርሐ ግብር አርሶ አደሩ የምርት ግብዓት ችግር እንዳይገጥመው በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

የዱግዳ ወረዳ አርሶ አደር አሰፋ ጉዳታ ቀደም ሲል በተናጠል የሚዘራው አዝመራ የግብዓት እጥረት፣ የጉልበትና ለብክነት ሲያጋልጥ የቆየ መሆኑን ተናግሮ፤ እርሱን ጨምሮ የወረዳው አብዛኛው አርሶ አደር በኩታ ገጠም በማረስ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆነ ተናግረዋል።

ዞኑ በበጋ መስኖም ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ላይ ስንዴ ልማት በማልማት ከ7 ነጥብ 2 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት አቅዶ እየተሠራ መሆኑን አቶ አባቡ ዋቆ ገልጸዋል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ የትግራይ ሕዝብ መከራ እንዲረዝም አይፈቅዱም!

ሀገርና ሕዝብን ከጥቃት ከመከላከል ጎንለጎን የኢትዮጵያ መንግሥት አሸባሪው ትሕነግ በሰሜን ኢትዮጵያ የፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ማድረጉን አጠናክሮ ቀጥሏል:: ይህንንም የሚያደርገው ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ የሚቻለው በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መንገድ ነው የሚል ጽኑ አቋም ስላለው ነው:: ይህንንም አቋሙን ተጨባጭ ርምጃዎችን በመውሰድ በተግባር አሳይቷል፤ ከሕግ ማስከበር ዘመቻ እንዲሁም ከሕልውና ዘመቻ በፊትም ሆነ በኋላ እንዲሁም አሸባሪው ቡድን በቅርቡ እንደለመደው ሦስተኛውን ጦርነት ከመከፈቱ በፊትም በኋላም እያረጋገጠ ይገኛል::

ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ እየሠራ ለሚገኘው የአፍሪካ ኅብረት ጥሪ አሸባሪው ቅድመ ሁኔታዎች እየደረደረ ባለበት ወቅት መንግሥት ምንም አይነት ቅደመ ሁኔታዎችን ሳያስቀምጥ ፈጥኖ አዎንታዊ ምላሾችን በመስጠት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት ሲያረጋግጥ ቆይቷል፤ አሸባሪው ቡድን የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን እየደረደረ ፤ለአፍሪካ ኅብረት ልዑክም ጥረት ዋጋ እያሳጣ ጥረቱን ሲያጣጥል በነበረበት ወቅት ሁሉ መንግሥት ለሰላም ያለውን ዝግጁነት ደጋግሞ በተግባር አረጋግጧል::

የመንግሥት ትዕግስትና ለሰላም ያለው ጽኑ እምነት ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል:: መንግሥት በደቡብ አፍሪካው የሰላም ንግግር እየተሳተፈ ያለው አሸባሪው ትሕነግ ለሶስተኛ ጊዜ የከፈተውን ጦርነት እየተከላከለ፣ ነጻ ባወጣቸው የትግራይ አካባቢዎች ያለው ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታዎችን እንዲያገኝ እያደረገ፣ ቡድኑ ባካሄዳቸው ጦርነቶች ከአገልግሎት ውጪ የነበሩ መሠረተ ልማቶችን በመጠገንና እንደገና አገልግሎት እንዲጀምሩ በማድረግ፣ ነጻ ከወጡ አካባቢዎች ማኅበረሰቦች ጋር በመነጋገር ሕዝባዊ አስተዳደር የሚቋቋምበትን ሁኔታ እያመቻቸ ባለበት ሁኔታ ነው:: ይህ ሁሉ እየተካሄደ የሚገኘው የሰላም ንግግሩ ውጤታማ እንዲሆን የጎላ ፋይዳ እንደሚኖረው ስለሚታመን ነው::

የሽብር ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ የፈየደው የለም:: ይልቁኑም በሚከፍታቸው ግጭቶችና ጦርነቶች ሰብዓዊ ጋሻ አርጎ ሲጠቀምበት ነው የኖረው:: ይህን ሕዝብ ከእዚህ የሽብር ቡድን መንጋጋ ማውጣት ያስፈልጋል::

የሽብር ቡድኑ ሦስት ጊዜ ጦርነት ከፍቶ ሀገርና ሕዝብ አድምቷል፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የትግራይን ሕዝብ ለመታደግ ሲል ብዙ ዋጋ ከፍሏል፤ እየከፈለም ነው:: ለሰላማዊ አማራጭ ሲባል ቡድኑ ያን ሁሉ ግፍ ፈጽሞም መንግሥት በጠረጴዛ ዙሪያ ለመነጋገር ብዙ ጥረት አድርጓል:: ወርቃማ ድሎች በእጁ ገብተውም ጦርነት ዘላቂ ሰላም አያመጣም በሚል ለሰላም ሲል የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል፤ የተናጠል ተኩስ አቁም አድርጎ ከትግራይ የወጣበት፣ በሕግ ጥላ ስር የነበሩ የቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች ክስ የተቋረጠበት፣ ቀደም ሲልም የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ እናቶች አምባሰደሮች ያደረጓቸው ጥረቶች ሁሉ ለሰላም የተከፈሉ ውድ ዋጋዎች ናቸው:: የሽብር ቡድኑ ሁሉንም ገፍቶ ነው ሦስት ጊዜ ጦርነቶች ከፍቶ ሀገርና ሕዝብን ታሪክ ይቅር የማይለው ግፍ የፈጸመው::

ይህን የቡድኑን ግፍ ደጋፊዎቹ አንዳንድ የውጭ ኃይሎችና መንግሥታት አሳምረው ያውቃሉ:: ይሁንና እነዚህ መንግሥታት ዛሬም እንደ ትናንቱ የተኩስ አቁም ይደረግ የሚል ሀሳብ እያቀረቡ መሆናቸውን ለከፍተኛ ትዝብት የሚዳርጋቸው ነው:: እነዚህ ኃይሎች የሽብር ቡድኑ ያሸነፈ ሲመስላቸው ነገሮችን በእርምሞ የሚመለከቱ፤ የተሸነፈ ሲመስላቸው ደግሞ የተኩስ አቁምና የመሳሰሉትን ጥሪዎች የሚያቀርቡ ናቸው::

ሞኝ አውሬ ነው በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ሁለቴ የሚወጋው ይባላል:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ሶስት ጊዜ ለወጋ ቡድን ከዚህ በላይ ዋጋ አይከፍልም፤ ከዚህ በኋላ የተኩስ አቁም ማድረግ የትግራይን ሕዝብም ለተጨማሪ ውስብስብ ችግር መዳረግ ይሆናል:: የትግራይ ሕዝብ ለአያሌ አስርተ ዓመታት በአሸባሪው ትሕነግ ታግቶ የኖረ ሕዝብ ነው፤ አሸባሪው ቡድን የትግራይን ሕዝብ እንደ ሰብዓዊ ጋሻ አርጎ ሲጠቅምበት ዘመናትን ዘልቋል፤ የትግራይ ሕዝብ ጫንቃ ከዚህ በኋላ እንዲህ ያለውን መጥፎ ቀንበር ሊሸከም ፈጽሞ አይችልም::

የትግራይ ሕዝብ ቡድኑ ሲመሠረት አንስቶ ብዙ ውድ ዋጋ ቢከፍልም፣ እየተንደላቀቁ ያሉት ግን ጥቂት በቤተሰብና ጓደኝነት የተሰባሰቡ የሽብር ቡድኑ መሪዎችና ተላላኪዎቻቸው ብቻ ናቸው:: የእነዚህ የቡድኑ ዘዋሪዎች ቤተሰቦች በአውሮፓ በአሜሪካ ሲንደላቀቁ፣ ለዘመናት በርካታ የትግራይ ሕዝብ ከሴፍቲኔት ፕሮግራም አልተላቀቀም:: ቡድኑ ይህ እንዲቀጥል ማድረጉ አልበቃ ብሎ ሦስት ጊዜ በከፈታቸው ጦርነቶች ይህን ሕዝብ የጥይት ቀለብ አርጎታል፤ ሕዝባዊ ማዕበል በሚለው ያረጀ ያፈጀ የጦርነት ዘይቤ ያስጨረሳቸው ሕጻናት፣ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች፣ እናቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ ቤቱ ይቁጠራቸው::

ቡድኑ የሚፈጽመው ግፍ መቆም ይኖርበታል፤ በዚህ ወቅት የተኩስ አቁም እንዲደረግ መጠየቅ ይህ ግፍ እንዲቀጥል መፍቀድ ይሆናል:: አሁን የሚሻለው፣ መሆንም ያለበት ቡድኑን ትጥቅ አስፈትቶ ንግግሩን አጠናክሮ መቀጠል ብቻ ነው:: ይህን ማድረግ ሲቻል የሰላም መንገዱ ፈር እየያዘና ውጤታማ እየሆነ ይመጣል::

ስለሆነም ስለተኩስ አቁም አጀንዳ የሚያራምዱ አካላት ለሕዝብ ጥቅም ሲሉ አጀንዳቸውን ማጠፍ ይኖርባቸዋል:: የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ በምንም ዓይነት መልኩ የትግራይ ሕዝብ መከራ እንዲረዝም አይፈቅዱም!


ኢፕድ

## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ለሰራዊቱ ክብር ሰጥተን፤ እጅ እንነሳለን!

**ሜሉዲ ከኳስ ሜዳ**

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት /የምድርም የአየርም / ለአገር ክብር የሚዋደቅ፣ ለሉአላዊነት የሚዘምት ሰራዊት ነው። ራሱን መስዋዕት በማድረግ ኢትዮጵያ ጸንታ እንድትቆም ያደረገ፣ አሁንም ቢሆን ለሕገ መንግሥት እንዲሁም ለሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ መከበር እየተዋደቀ የሚገኝ ነው።

በሕዝባዊነቱ የማይታማ፤ በተሰማራባቸው የግዳጅ ቀጣናዎች ጀብዱዎችን በመፈጸም ታሪክ የሚዘክረው ሰራዊት ነው። በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ረሃብ እና ጥማት ሳይበግረው ረጅም ኪሎሜትሮችን በእግሩ እየተጓዘ የኢትዮጵያን የጽናት ታሪክ በወርቃማ ቀለም ያስመዘገበ፤ እያስመዘገበ ያለ ሰራዊት ነው ።

ለውጡን ተከትሎ ‹‹ሰራዊት አገር እንጂ ብሔር የለውም›› በሚል መርህ በጠንካራ ሕዝባዊነት ላይ በመመስረት የተሰጠውን እና የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ተልዕኮ እየተወጣ የሚገኝ፤ ኢትዮጵያዊ መልክ ያለው ሙያውን የሚያከብር ጠንካራ ሰራዊት ነው። ለዚህ ደግሞ ከፍ ያለ ምስጋናና እውቅና ሊቸረው ይገባል።

አሸባሪው እና ከሀዲው ትህነግ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ዘግናኝ ጥቃት ፈጥኖ እራሱን አደራጅቶ በመቀልበስ አገርንና ሕዝብን ከጥፋት መታደግ የቻለ፤ በዚህም የአገርና ሕዝብ ኩራትነቱን በተጨባጭ ያረጋገጠ ጀግና ሰራዊት ነው።

የአስተሳሰብ መሠረቱ የሆነው ሕዝባዊነቱን በየትኛውም ሁኔታ ለድርድር የማያስቀምጥ፤ ይህንን ባህሪውን የሚፈታተኑ ተግዳሮቶችን መሻገር በሚያስችል ስብእና የገነባ፤ በዚህም የማይታማ ልበ ሰፊ፤ በከፍተኛ ዲሲፕሊን የተገነባ ሰራዊት ነው።

ስለ አገሩ ሉአላዊነትና ከዚህ ለሚመነጨው ክብሩ ጥልቅ ዋጋ ከሚሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ የወጣው፣ አገር ችግር ላይ ወድቃለች ሲባል ጨርቄን ማቅን ሳይል ለአገሩ ክብር እና ሉዓላዊነት በጀግንነት የሚዋደቅ የኢትዮጵያዊነት ምልክት! የአገር መለያ አርማ ነው። ለዚህ ሰራዊት አባላት ከፍያለ ክብር ይገባቸዋል። ሞተው ኢትዮጵያን ስላጸኑ፤ ደማቸውን አፍስሰው ሕዝብን ነፃ ስላወጡ ለእነዚህ ጀግኖች እጅ እንነሳለን!።

**አሸባሪው እና ከሀዲው ትህነግ ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ዘግናኝ ጥቃት ፈጥኖ እራሱን አደራጅቶ በመቀልበስ አገርንና ሕዝብን ከጥፋት መታደግ የቻለ፤ በዚህም የአገርና ሕዝብ ኩራትነቱን በተጨባጭ ያረጋገጠ ጀግና ሰራዊት ነው**

• • • • •

ሰራዊቱ ከአንዴም ሁለት ሦስት ጊዜ አሸባሪው ትህነግ በአገርና በሕዝብ ላይ የከፈታቸውን የእብሪት ጦርነቶች በመመከት ፤ በታላቅ ጀግንነት የቡድኑን ከንቱ ህልም ወደ ቅዥት በመለወጥ የአገር መመኪያነቱን በተግባር አስመስክሯል።

ኢትዮጵያን እንደ ሶሪያ፣ ሊቢያ፣ አፍጋኒስታን፣ ኢራቅ፣ የመን ለመበታተን በውስጥ በውጭ ኃይሎችና በውስጥ ባንዳዎች የተሸረቡ አደገኛ ሴራዎችን በብዙ መስዋእትነት በመቀልበስ የሕገመንግሥቱ ዘብ መሆኑን በመስዋእትነቱ አስመስክሯል።

ዛሬም የትግራይን ሕዝብ ከአሸባሪ ትህነግ የግፍ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በታላቅ ተጋድሎ ላይ ይገኛል። ይህ ከሕዝባዊነቱ የሚመነጨው ነፃ የማውጣት መስዋእትነት ጉዞ በቀጣይ በትግራይ ሕዝብ ዘንድ ሊፈጥር የሚችለው እፎይታ በታሪክ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ሊያገኝ እንደሚችል ይታመናል።

የዓባይ ግድብን ጨምሮ ሌሎች የተገነቡና በግንባታ ላይ የሚገኙ ታላላቅ ፕሮጀክቶችንም ከማንኛውም ጥቃት በአስተማማኝ መልኩ በመጠበቅ ልማት እንዲረጋገጥ ያስቻለ ሰራዊት ነው።

በውስጥና በውጭ የነበረውን ከፍተኛ ጫና በመመከት ኢትዮጵያን እንደ አገር ማስቀጠል ችሏል። የሰራዊቱ የግዳጅ አፈጻጸሙ፤ ምኞቱ፣ ፍላጎቱ፣ ግቡም አገርን የማስቀጠል ዓላማ ያነገበ በዚህም ሕዝባዊነቱን ማስመስከር የቻለ ነው።

ሰራዊቱ በወታደራዊ ዲሲፕሊን በእውቀት ክህሎትና ቴክኖሎጂ እራሱን በተሻለ መልኩ አደራጅቶ የትኛውንም ዓይነት ጠላት ሊመክት የሚችል ቁመና ተላብሷል፣ በጠንካራ ሥነ ልቦ የተገነባም በመሆኑ የግዳጅ አፈጻተሙ ከትናንት ዛሬ፤ ከዛሬ ነገ አስተማማኝ እየሆነ በሚሄድበት የጥንካሬ ጎዳና ላይ ነው።

ሰራዊቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታወቅበት ጉዳይ አንዱ በስነ ምግባሩ ነው። ቀደም ባለው ዘመን በኮሪያ እና ኮንጎ በቅርቡም በሩዋንዳ፣ በሱዳን፣ በሶማሊያ---ወዘተ የተሰጠውን የሰላም ማስከበር ግዳጅ ባግባቡ የተወጣ፣ በዚህም መልካም ስም ያተረፈ ነው።

በሕዝብ ፊትም ሰንደቅ ዓላማ ይዞ ስለአገሩ ዘብ ለመቆም ቃል የገባ ለአገሩ፣ ለሕዝቡ እንዲሁም ለሕገ መንግሥቱ ተጠሪ ሆኖ እየሠራ ያለ ነው። በቃሉ ተፈትኖ ፀንቶ መቆም የቻለ ሰራዊት ነው።

ሰራዊቱ ሕዝባዊም ነው። ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ጤና ተቋም እና ትምህርት ቤቶችን በየአካባቢው የሚገነባ። በእርሻ ወቅትም አርሶ አደሩን የሚያግዝ፣ በዚህም ሕዝባዊነቱን በተጨባጭ ያረጋገጠና እያረጋገጠ ያለ ሰራዊት ነው። ለዚህ ሰራዊት እና ለአባላቱ ከፍያለ ክብር ይገባቸዋል።

የትኛውንም የአገርና የሕዝብ ጠላት ሊመክት የሚችል ቁመና የተላበሰ እና ኢትዮጵያውያንን ያኮራ ሰራዊት ነው። ሕዝብን ነን የማውጣት ተልዕኮውን በድል እየተወጣ የሚገኝ፣ ራሱ እየሞተ ወገኑን ያዳነ፣ አገር እንድትቀጥል እያደረገ የሚገኝ ነው። ለዚህ ጀግና ሰራዊት ክብር ሰጥተናል፣ እጅ ነስተናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ሲነጋጋ የወፎቹ ጫጫታ ከዚህና ከዚያ

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ)**

‹‹ሊነጋ ሲል ይጨላልማል›› የምትል አንድ አባባል አለች። እውነት ነው ንጋት ላይ ይጨልማል። ኸረ ደረቅ ጨለማ ብቻም አይደል ! ብርድም አለ፤ ከፍተኛ ቅዝቃዜ። ሆኖም ግን ብዙ ሰዓት አይዘልቅም። ጨለማው እየገፈፈ፣ ብርዱም እየለቀቀ ፣ ጤዛውም እየረገፈ ይሄዳል። ውርጩ ቀለል እያለ የአእዋፋት ጫጫታ አየሩን ይሞላል፤ የወፎቹ ዝማሬ ንጋትን ያበስራል። በመጋረጃው ጀርባ በመስኮቱ ጭላንጭል ሲያይ ያንቀላፋው ሰውነት ይነቃቃል። ምክንያቱ ብርሀኑን ማየቱ ነዋ ።

ያኔ ታዲያ በእንቅልፍ ጭፍግግ ያለው ሰውነትም እየተፍታታ፣ ፊትም ይፈካል። በቀዝቃዛው ሰማይ ላይ በምሥራቁ ክፍል ፍንጥቅ ብላ የወጣችውን የፀሐይ ጮራ ላየ ተስፋው ይለመልማል።... በንጋት ውስጥ ብዙ ነገር አለ። ብዙ ሥራ ይሠራል መልካም... መልካም...። ብርሀናማው አየር ተስፋ ብቻ ሳይሆን ብዙ ራዕይ ያሰንቃል። ለዓላማ በዓላማ ያሠራል። ምቹ አየር ካለ፣ ምቹ ስፍራ ከተገኘ፣ ተስፋ ያደረገ ሁሉ ተስፋው አብቦና አፍርቶ ያየዋል። ለሁሉም ግን የሚያስፈልገው ቀን ነው ፤ ብርሀኑ ከዳር ዳር የሚያበራ ቀን፤ ቀኑን ቆጥሮ ጠንከር ብሎ ተስፋውን ወደ ፍሬ መለወጥ የሚችል ቆራጥና ቆፍጣና።

ዛሬ በትግራይ ያለው ሁኔታ ይህን ይመስላል። የትግራይ ሕዝብ ንጋት ላይ ነው። የደበዘዘው ተስፋ አሁን መነቃቃት ይጀምራል፤ ተስፋ የቆረጠው ሕዝብ የተስፋ ጭላንጭል ማየትና ማለም ይቀጥላል። የነገዋን ፀሐይ ለማየት የደመነውን ፊቱን በሀሴት ለመቀየር ጊዜው ተቃርቧል። ጭለማው ዛሬ ላይ ወደ ሰሜን እያዘቀዘቀ ይገኛል። የጭለማው ጊዜ በብርሀን ሊተካ ወጋገን ላይ ቆሟል።

የትግራይ ሕዝብ ጨለማ ውስጥ የገባው ዛሬ አይደለም። የትግራይ ሕዝብ ድቅድቅ ጨለማ የገባው አሸባሪው ትህነግ የሰሜን እዝ ሰራዊት ላይ ጥቃት የፈጸመ ዕለት ነው። ብርድ አይንካህ ወገኔ፤ ዝናብና ፀሐይ አይፈራረቅብህ ወንድሜ ብሎ ቤቱን ሲሠራ፣ አይራብህ አይጥማህ ብቻህን አትድከም ብሎ አብሮት ማሳ ለማሳ ሲያጭድና ሲከምር፤ አንበጣ ሲያባርር፤ የውሀ ጉድጓድ ሲቆፍር ኖሮ የተከዳ ዕለት ነው።

የድህነት ማባረሪያው፣ የክፋት ማሰሪያው ትምህርት ቤት ነው ብሎ በገዛ ገንዘቡ ትምህርት ቤት ሲገነባለት የኖረው የመከላከያ ሰራዊት ላይ አሸባሪው ቡድን ቃታ የጎተተ ቀን ነው የትግራይ ሕዝብ ጨለማ የገባው። በላዩ ላይ ጭካኔ በሞላ ሁኔታ ሲኖትራክ የተነዳበት ጊዜ ነው። ልብሱን አስወልቆ ራቁትን በረሀ ለበረሀ የበተነው ጊዜ፤ የአገሩ ሰንደቅ ያረፈበትን የመከላከያ ሰራዊት ልብስ ሜዳ ለሜዳ የጎተተ ጊዜ ነው። ያኔ ነው የኢትዮጵያን ክብር አዋረድኩ ብሎ ክብሩን ያወረደው። ያኔ... ያኔ ነው አሸባሪው ትህነግ የትግራይን ሕዝብ ጨለማ ውስጥ ያስገባው። የመከላከያ ሰራዊትን እጅ አመድ አፋሽ ፤ ልፋቱን ከንቱ ያደረገበት ውለታ ቢሱ ትህነግ የከዳው ዕለት ነው የትግራይን ሕዝብ ጨለማ ውስጥ የጣለው።

አሸባሪው ትህነግ እኮ የትግራይን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የመላውን ሕዝብ ሰላም ያደፈረሰው፣አንድነቱን ለማናጋት የሞከረው፤ ኢኮኖሚውን ያንገዳገደው ዛሬ አይደለም። አገር አፈርሳለሁ ብሎ ሲደሰኩር፤ የአማራና የአፋር ሕዝብን ሲወርና ሲጨፈጭፍ ነው። በአማራ ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ሲፈጽም፣ በጅምላ መቃብር ሲያዳፍን፤ ከሕፃን እስከ አዛውንት ሲደፍርና የሀገርን ባህልና ታሪክ ሲያጎድፍ፤ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ቆሞ የባንዳነት ተግባሩን ሲከውን ነው። ተላላኪነቱን ተቀብሎ አገር የከዳ ጊዜ ነው።

የትግራይን ሕዝብ ከሌላው እህት ወንድም ወገኑ ሊነጥለው ፤ ‹‹የትግራይ መንግሥት አቋቁማለሁ፤ ምርጫ በራሳችን፤ በሕገ መንግሥቱ አንተዳደርም›› ብሎ ጡንቻ እንለካካ ያለጊዜ ነው። ያኔ ነው ጨለማ ውስጥ የከተተው የትግራይን ሕዝብ።

**የትግራይ ሕዝብ በመሠረተ ልማቶቹ እንዳይጠቀም ኤሌክትሪክ እንዳያገኝ፣ የገንዘብ ዝውውር እንዳይኖረው፣ የመገናኛ አውታሮች እንዳይሠሩ መሠረተ ልማቶችን ሲበጣጥሳቸው፣ ሲንድና ሲያፈርሳቸው፤ ሲዘርፍና ሲያወድማቸው ያኔ ነው የትግራይ ሕዝብ ጨለማ የገባው። በጠላቱ በትህነግ ሴራ ሲሠራበት። እንዲራብና እንዲጠማ ያለዳኛ ሲፈረድበት፤ ያኔ ነው የትግራይ ሕዝብ በድቅድቁ ጨለማ የወደቀው**

‹‹አማራ ጠላትህ ነው››፤ ‹‹ሂሳብ እናወራርዳለን›› ብሎ ሲደሰኩር ተጋብቶ፤ ተዋልዶ በፍቅር የኖረውን ሕዝብ እርስ በእርሱ ሲያባላው ከርሟል። ግን እኮ በዚህ ሰበካው ሕዝብን ከሕዝብ አባላ እንጂ አሁን አሁን ደግሞ ትርክቱን ወደ መዋጥ እየገባም ነበር። አማራ ወንድም ነው፤ አማራ እህት ናት፤ ከአንተ ከአንቺ ጸብ የለንም እያለ ሊሰብከም ሞክሯል።‹‹የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ›› የምትል አንድ አባባል አለች አይደል የትህነግ ቅጥፈት፣ ፕሮፖጋንዳ እና ትርክት ያቺን አባባል እንዳስታውሳት አስታውሼም እንድከትባት ገፋፋኝ።

የትግራይ ሕዝብ በመሠረተ ልማቶቹ እንዳይጠቀም ኤሌክትሪክ እንዳያገኝ፣ የገንዘብ ዝውውር እንዳይኖረው፣ የመገናኛ አውታሮች እንዳይሠሩ መሠረተ ልማቶችን ሲበጣጥሳቸው፣ ሲንድና ሲያፈርሳቸው፤ ሲዘርፍና ሲያወድማቸው ያኔ ነው የትግራይ ሕዝብ ጨለማ የገባው። በጠላቱ በትህነግ ሴራ ሲሠራበት። እንዲራብና እንዲጠማ ያለዳኛ ሲፈረድበት፤ ያኔ ነው የትግራይ ሕዝብ በድቅድቁ ጨለማ የወደቀው።

አሸባሪው ትህነግ በወሬው ‹‹የቆምኩት ለአንተ ነው ፤ ነፃነትህን ላስከብር ነው›› የሚለውን የትግራይ ሕዝብን ያሰቃየውና አይበድሉ በደል ሲበድለው የቆየው አሁን ብቻ አይደለም። በ1977 ዓ.ም የትግል ወቅት በሚለው ሰዓትም የትግራይ ሕዝብ በረሀብና ችግር ሲፈተን ትህነግ ለሕዝቡ የቀረበን ሰብአዊ እርዳታ እየቸበቸበ የመሣሪያ መግዣ ሲያውለው ነበር።

ይህን የትግራይ ሕዝብ ጥንቅቅ አድርጎ ያውቀዋል። በወቅቱ ታጋይ የነበሩት በየአደባባዩ መስክረዋል። ዓለም አቀፍ ተቋማት ማረጋገጣቸውን አሳውቀዋል። ይሄ ከስህተቱ የማይማር የሰዎች ችግር ደስታው፤ የሰው ኀዘን ዳንሱ የሆነ ቡድን ግን አሁንም እየሠራ ያለው ዳግም ጥፋት ነው። አሁንም ከዚሁ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቱ ሳይማር ድጋሚ ይሄንኑ በተግባር አሳይቷል።

ለትግራይ ሕዝብ የመጣን ሰብአዊ እርዳታና መድኃኒት ለሕዝቡ ሳይሆን ለወታደራዊ አገልግሎት ሲያውል በአደባባይ ታይቷል። መጋዘን እየዘረፈ የሕፃናትን አልሚ ምግብ ለወታደሩ ቀለብ አድርጎታል። እርዳታ ለሕዝቡ እንዳይዳረስ ሰብአዊ እርዳታ ይዘው የገቡ መኪኖችን የጦር መሣሪያ መጓጓዣ ሲያደርግና ነዳጅ ሲዘርፍ ዓለምአቀፉ ተቋማትና መገናኛ ብዙኃን ጭምር አጋልጠውታል።

ቅጥፈትና ስርቆት መለያው የሆነው አሸባሪው ቡድን ይሄን ብቻ ግን አይደለም በትግራይ ሕዝብ ላይ የፈጸመው በደል፤ ገና ነገ የሚሰሙ ዛሬ የተደበቁ ግፎች ሁሉ እንደሚኖሩ ይታሰባል። የታሰረው እና የታፈነው ትግራይዋይ ሲነጋለት በደሉን ፀሐይ ያሞቀዋል። ይሄ እንደሚሆን እንጠብቃለን። ምክንያቱም አመላካች ነገሮች ተሰደው የመጡት፤ ከድውና ተማርከው የገቡት ሁሉ እየተናገሩና እየመሰከሩ ያሉት ይሄንኑ ኢ-ሰብአዊ ባህሪውን ነው። ለውትድርና በግድ የመለመለውን ያለ ዕድሜው ለጥይት የዳረገው ሕፃንና ወጣት ሰውነቱ ባይጠና አእምሮው አልቀበል ሲለው ወደኋላው ሲመለስ የሚጠይቀው የትህነግ ጥይት ነው። ወደፊት ተማገድ እንጂ ወደኋላ እንዳትዞር የሁልጊዜም ማስፈራሪያ ነው። ይህን ያልፈጸመ ለሌሎች መቀጣጫ መሆኑ አይቀሬ ነው። እናም ሕፃን ወጣቱ ሁሉ ከፊት ከኋላ ጥይት ሆኖ ተቀባዩ እናቶች ያለ ጧሪና ቀባሪ እንዲቀሩ ተገደዋል። ያ ሁሉ የረገፈ ወጣት የት ገባ ብሎ ይደሰኩር ይሆን? መቼም እንደጥቂቶቹ ልጆች የእነሱም አውሮፓና አሜሪካ ለትምህርት ሄደው እንደማይሆን ልጆቻቸው ለጥይት ሲሳይ የሆኑባቸው እናቶች ልቡና ያውቀዋል። እነሱ ያለቀሱት ፤ ያረረና የተኮማተረ አንጀታቸውን በመቀነት ያጠበቁት ያኔ ነው፤ ያኔ ትህነግ ከስልጣን ተባሮ መቀሌ ሲከትም፤ላወጣው ሕገ መንግሥት አልገዛም ብሎ ሲፎክር ነው። ቀጥሎ ለስልጣኔ ማስመለሻ ልጆቻችሁን ለጥይት ገብሩ እንደሚላቸው ከኖረው ባህሪው ያውቁታል። አውቀው ችለውታል፣ መቼ ይሆን ከጫንቃችን መውረጃው ነበር ህልማቸው።

አሁንም ግን የትግራይ ሕዝብ ስቃይ አልበቃም፤ ከችግሩ ተላቆ ገና ነፃ አልወጣም። አሁንም በትህነግ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ እንዲሁም ተገዶ ልጁን ዓላማ ለሌለው ጦርነት የዳረገው ብዙ ሰው ነው። በመማሪያ ዕድሜያቸው ለማያምኑበት ጦርነት ተገደው የገቡ በሞት የጥይት እራት የሆኑ ሕፃናትና ወጣቶች ብዙ ናቸው። እናት አንጀቷን አስራ ተቸግራና ተሰቃይታ ያሳደገቻቸውን ሴት ወንድ ሳትል ልጆቿን አሳልፋ የጥይት ማብረጃ፤ ለአፈር ለግሳለች። ዛሬ ልጆቼ ያሳልፉልኛል፤ ይደግፉኛል የሚል ተስፋ የላትም። ይሄ ሁሉ በትህነግ የማያባራ ሴራ የተፈጸመ ግፍ ነው።

በችግርና በጦርነት ከሚሰቃየውና ከሚሞተው የትግራይ ሕዝብ ጎን ለጎን ሕፃናት ትምህርት እንዳይማሩ ሆነዋል። ሮጠውና ቦርቀው፤ ፊደል በመጨበጫ እድሜያቸው ጉልበታቸውን ታቅፈው ቆዝመው እንዲቀመጡ ተገደዋል። ‹‹ነፃ እናወጣችኋለን›› ፕሮፓጋንዳ የዕለት ምግባቸው ሆኖ ቆይቷል። የትግራይ ሕዝብ አስከፊ የሆኑ በደሎች ሁሉ ቀምሷል። ተስፋቸው ጨለማ፣ ኑሮው ስቃይ ሆኖ ከርሟል፤ አሁን ግን ይሄ አስከፊ ዘመን የሚቋጭበት ዳር ድንበር ላይ ደርሷል።

‹‹ነፃ አወጣሀለሁ›› የሚለውን ነፃ ያልወጣ ቡድን በቃህ የሚሉበት ወቅት ላይ ደርሰዋል። ለራሱ ከሴራ ፖለቲካ ነፃ ያልወጣ ነፃ አውጪ በአንድ ቤተሰብ የተሰባሰበ ነፃ አውጪ ነፃ እንዲያወጣው የትግራይን ሕዝብ የሚያሰቃይ የስም ነፃ አውጪ መሆኑን አሁን መረዳት የሚቻልበት ወቅት ላይ ደርሷል። ነፃ የሚያወጣው የአንድ ቤተሰብ አባላትን በስልጣን ላይ እያስመረቁ በፌስቡክ ምርቃት የሚጠሩትን አካል መሆኑን በትክክል መገንዘብ ችሏል።

አሁን ነፃ የሚያወጣው የአራት ኪሎ ስልጣኑን ለማስመለስ አማልዱኝ፣ እርዱኝና ድረሱልኝ የሚለውን አካል መሆኑን አውቋል። እስካሁንም ሆነ ወደፊት ለሕዝቡ እንዳልቆመ ከድርጊቱ ለማወቅ ችሏል። አሁን የትግራይ ሕዝብ መካሪ አይሻውም። ችግር መክሮታል። አታላይ አያታልለውም፤ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የት እንዳደረሰው የተነገረና የተሞላው ሁሉ ከአገሩና ከወገኑ የሚያለያየው እንጂ የሚያፋቅረው እንዳልሆነ በተጨባጭ አረጋግጧል። ከኢትዮጵያዊ ወገኑ ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረ ወንድሙ መሆኑን አሁንም በስደቱ ወቅት አይቶታል። ማነህ አንተ ማነሽ ብሎ ፊቱን ያዞረና የተበቀለው የለም፤ ምክንያቱም ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ጸብ የለውም። ይልቅስ ወገኔ ብሎ አቅፎታል፤ ቁርሶ አጉርሶታል። ጉሮሮውን በውሀ አርጥቦ ማረፊያ ሆኖታል። ኢትዮጵያዊ ይሄ ነውና።

ጥቂቶች ለስልጣናቸው፣ የሰረቁት ሀብት እንዳይወረስ የትግራይ ሕዝብ እንደ ትናንቱ ሁሉ ሊደልሉት ይከጅላሉ። ዛሬ የሚሞኝና በሀሰት ልምጭ የሚነዳ ሕዝብ አይደለም። ቆሞ ያስባል፤ አስቦ ይራመዳል። ተራምዶም መብቱን ያስከብራል። ከትህነግ የኢ- ሰብአዊ ድርጊት ራሱን ነፃ ያወጣል። ለዚህ ደግሞ አሁን ጊዜው ደርሷል። ሊነጋጋ ሲል ይጨልማል እሚባልበት ደረጃ ላይ ይገኛል። የወፎቹን ድምጽ ሰምቶ ለማጣጣም፤ አጣጥሞ ብርሀኑን ሊያይ በብርሀኑም ሊመላለስ ጊዜው ደርሷል።

ሊነጋ ሲል እንደሚንጫጬት አእዋፋት ሁሉ ለትግራይ ሕዝብም ሊነጋለት ሲል ጫጫታው በዝቷል። ከዚህም ከዚያም ጩኸቱ ደርቷል። ሆኖም እውነቱን ከሀሰት፤ ከሀዲውን ከእውነተኛው መለየት የሚችለው መከራውን የቀመሰው ሕዝብ ነው። በቆየበት የመከራ ጊዜ ይሄንን ለመለየት ይችላል። አስከፊ የጨለማ ዓመታት በቅቶት በብርሀማው ዘመን እንዲተካ አሁንም የትግራይ ሕዝብ ከሀሰተኛው ፕሮፓጋንዳ መባነን አለበት። አሁን የንጋቱ ደውል ተደውሏል፤ የወፎቹን ጫጫታ ማድመጥ ትቶ የተኛውም ይንቃ። በብርሀኑን ይመላለስ። አበቃን !።

# ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው «ደቦ»

ግርማ መንግሥቴ

ግብርና ለሰው ፍጡር ሁሉ ህልውና ነው። ህልውና ይሆን ዘንድ ግን ሂደቱም ሆነ አሠራሩ የዋዛ አይደለም። ሁላችንም እንደምናውቀው እጅግ ከባድና በገበሬው ላይ የወደቀ ኃላፊነት ነው።

ይህ በአርሶ አደሩ ትከሻ ላይ የወደቀ ኃላፊነት እንደኛ ላሉ አገራት ሁሉ ነገራቸው ሲሆን፤ በተለይም ኢኮኖሚውን ቀጥ አድርጎ የያዘው መሆኑ በራሱ ማስረጃ ነውና ስለ አተገባበሩ ማውራት ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም።

እርግጥ ነው፣ ይህንን ከባድ ማህበራዊና አገራዊ ኃላፊነትን የተሸከመው ገበሬ የዋዛ አይደለም። የዋዛ አለመሆኑ ማሳያው ደግሞ የዋዛ ያልሆነውን ተግባር የሚያከናውነው የዋዛ ባልሆነ ቴክኒክና ታክቲኮች መሆኑ ነው፤ እሱም በደቦ ሥርዓት።

ካህሳይ ገብረእግዚአብሔር ከ«ባህላዊ ማህበራት» ዐቢይ ምድብ ስር የሚያካትቱት ደቦ - በግብርና ሥራ ጊዜ ተሰባስቦ እርዳታን መለዋወጥ («እገሌ የእኽል አጨዳ ደቦ አለበት» እንደሚባለው ማለት ነው)፤ ብዙ ሰው ተሰብስቦ ለአንድ ሰው የሚሠራበት የኅብረት ሥራ፣ ደቦ የተወጣላቸው (ሥራው በደቦ የሚሠራላቸው) ሰዎች ድግስ እየደገሱ ተሳታፊውን እያበሉ፣ እያጠጡ የሚከናወን ተግባር ነው።

ቃሉ ከኦሮሚኛ የሆነው ደቦ በተለያዩ ተዛማጅ ስያሜዎችም የሚታወቅ ነው፤ ጂጊ፣ ወንፈል ... እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ደቦ «ወንፈል» ማለት ነው። ወንፈል ደግሞ ፍችው «አንድነት የሚታይበት የህብረት ሥራ ማህበር» ማለት መሆኑ ነው በስፋት የሚታወቀው። («ወንፈል»ን መዝገበ ቃላቱ ሲፈታው «ርስ በርሱ አንድ ቀን ላንዱ አንድ ቀን ለሌላው እየ ተወናፈሉ በማኅበር፣ በአንድነት፣ በተራ በተራ መሥራት ወንፈል ይባላል።» በማለት ሲሆን፤ በእንግሊዝኛውም communal labor, agricultural activity conducted by assisting one another በማለት ያስቀምጠዋል።)

ደቦ በአንድና ሁለት የአገራችን ክፍሎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ስሙና ስያሜው ይለያይ እንጂ በሁሉም የአገራችን ክፍሎች ተግባራዊ ሲደረግ የኖረና እየተደረገም ያለ ማህበረ-ባህላዊ እሴት ነው፤ ይህ ካህሳይ በ«ባህላዊ ክርስቲያናዊ ትውፊት በኢትዮጵያ» መጽሐፋቸው ያረጋገጡት፤ በትግራይ «ወፈራ» መባሉን በማሳያነት የጠቀሱለት በኅብረት የመሥራት ዘዴ ነው። ይህ ማለት፣ ደቦ፣ ጂጊ ወይም ወንፈል በገጠራማው የኢትዮጵያ ክፍል በጋራና በመተባበር ሥራ የሚሠራበት ባህላዊ ሥርዓት ነው።

ሰዎች፣ በተለይም በግብርናው ዘርፍ በእርሻ፣ በዘር፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅት የአካባቢው ኅብረተሰብ ጉልበቱን (ከነመሣሪያው) በማዋጣት ደቦ የጠራውን ሰው ይረዳል። ለምሳሌ፣ ለግለሰቡ ገበሬ ረዥም ጊዜ ሊወስድበት የሚችለውን የግብርና ሥራ (ለምሳሌ አጨዳ) በርካታ ሰዎች በአንድ ቀን ያጠናቅቁለታል ማለት ነው። በአንድ ሰው ጉልበት ብቻ ለማቃለል የማይችልን የግብርና ሥራ በተባበረ ክንድና በጣም በአጠረ ጊዜ የማጠናቀቂያ አገር በቀል የአሠራር ሥርዓት ነው።

ግብርና ላይ አተኮርን እንጂ ከእርሻ ሥራ ውጪም ለሌሎች ተግባራት ለምሳሌ ቤት መሥራት፣ ለቀብርና ለሰርግ ... ወዘተ ድንኳን ለመደኮንና የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ደቦ ሊጠራ ይችላል። ይህ በተለይ በአማራ ክልል አካባቢ በስፋት የሚሠራበት አሠራር (የኅብረት ሥራ) ነው።

በደቦ የሚሳተፉ ሰዎች እንደየ አካባቢው ሁኔታ የሚለያዩ ሲሆን፣ አንዱን አካባቢ በደቦ ሥራው የሚሠራለት ሰው ወገኖች (ዘመዶች) ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ አካባቢዎች ግን የአካባቢው ሰውና ሙያው ያለው ሁሉ የሚሳተፍበት ተግባር ነው።

ዝቅ ብለን የምንጠቅሰው ምንጫችን እንደሚያመለክተው ደቦ እንደ ዕድርና እንደ ዕቁብ በተወሰኑ ቋሚ አባላት አይመሠረትም፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ወዳጅነትና ቀረቤታ ወይም ዝምድናና አግባብ ያላቸው ሰዎች አንድን በርከት ያለ የጉልበት ኃይል የሚጠይቅ ተግባር ለአንድ የማኅበረሰቡ አባል በጋራ የሚያከናውኑበት ተቋም ነው፡፡ በማኅበረሰብ አባላት መካከል ካለው መጠቃቀም አንፃር ደቦ ልዩ ልዩ መልኮችና አፈጻጸሞች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ዋና ዋናዎቹ መገለጫዎች፣ ደቦ እንደ ጉልበትና አገልግሎት ልውውጥ እንዲሁም እንደ ማኅበራዊ የጉልበት ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት የሚኖረው ጠቀሜታዎች ናቸው፡፡

ደቦም ሆነ ወንፈል ወይም ጂጊ በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች እንደ መኖሩ ሁሉ በአማራም የሚዘወተርና በችግር ፈቺነቱ ታምኖበት ለዘመናት ሲሠራበት የቆየ የኅብረት አሠራር ነው።

ከክልሉ በተለያዩ ጊዜ የወጡ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከአማራ ሕዝብ የሥራ እሴቶች መካከል አንዱ ደቦ ነው። አርሶ አደሮች በአንድነት የሚረዳዱበትና የሚደጋገፉበት የመተጋገዝና መረዳዳት ባህል፤ ሥራን በጋራ የማከናወን ሂደት ነው። እንደየ አካባቢው ደቦ፣ ወንፈል፣ ወንበራ፣ ጅጌ እየተባለም ይጠራል። ሥራው በአረም፣ በእርሻ፣ በአጨዳ፣ በውቂያ፣ በቤት ሥራ፣ በእርከን ሥራ . . . ወዘተ የሚከወን ሲሆን፤ በሥራው ጊዜም ቀረርቶ(ሽለላ)፣ ፉከራ፣ የልጃገረዶች ዘፈን ይቀርባል፤ በስነቃል እና ዘፈን ታጅበው የደቦ፣ ወንፈል፣ ወንበራ እና ጂጊ (ጂጌ የሚሉም አሉ) ሥራቸውን ይከውናሉ።

አንድ የቦረና ሳይንት ነዋሪ እንደገለፁት በቦረና ሳይንት አማራ አንድ ጉብል ከታጨለት በኋላ ከሰርጉ በፊት አዝመራ ከደረሰ ባልንጀሮቹን በማሰባሰብ «የአምቻ አጨዳ አስተጫጭዱኝ» በማለት ይዞ ሄዶ የአማቾቹን ማሳ ያሳጭዳል። ሲጨርሱም ወደ ቤት ይጋበዛሉ፤ ይበላል ይጠጣል ... ሆታውም ይቀልጣል።

ካህሳይ ገብረእግዚአብሔርም ሆኑ ሌሎች እንደሚስማሙበትና እንዳሰፈሩትም የደቦ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታው ... ምርታማነትን (ውጤታማነትን) መጨመር፣ ጊዜን መቆጠብ፣ ማህበራዊ ሕይወትን ማጠናከር፣ የሥራ ላይ ድብርትንና ድካምን ማስወገድ ...፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሥራን በወቅቱ ማድረስ ነው። «በወቅቱ ...» ሲባል፣ ለምሳሌ ሰብል ሳይሰበሰብ ዝናብ ቢመጣ ሊያበላሸው ስለሚችል ያ ችግር ከመድረሱ በፊት ሰብል እንዲሰበሰብ ማድረግ ማስቻሉ ነው። ይህ ደግሞ ከላይ እንዳልነው፣ በግብርናው ዘርፍ የሞትና ሽረት ጉዳይ ስለሆነ ደቦን እጅጉን ተፈላጊ ያደርገዋል።

አስቀድመን «ደቦ በዘመናዊ አጠራሩ ኅብረት ሥራ ማለት» ነው ብለን ነበር። ኅብረት ሥራ ማለት («ዓለም ፊቷን ወደ ኅብረት ሥራ ማህበራት አዙራለች» በሚል ርእስ ለንባብ የበቃ ጽሑፍ እንደሚያሳየው) ደግሞ፤

የኅብረት ሥራ ማህበራት በጋራ ትብብር ላይ በመመሥረት ያለ ምንም (ጾታ፣ ሃይማኖት ...) ሳይለዩ አባሎቻቸውን አንድ ላይ በማቀፍ በዴሞክራሲያዊ መርህ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ሲሆኑ፣ በአንድ በኩል ትርፋማነትን እያራመዱ በሌላ በኩል ደግሞ ሰብአዊነትን የሚያራምድ አደረጃጀት ያላቸው ተቋማት ናቸው።

ማህበራቱ የአባሎቻቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያና ባህላዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት የሚንቀሳቀሱም ጭምር ናቸው። (ይህ በበኩሉ የአገራችንን የኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር 985/2009ን ያስታውሰናል።)

ከአንድ አመት በፊት ሪፖርተር ጋዜጣ «አገር በቀሉ ደቦ» በሚል ርእስ ስር ባሰፈረው ጽሑፍ «በገጠር የሚዘወተሩና የተለመዱ፣ የተጻፈ ደንብና መመሪያ ሳይኖራቸው በጋራ ስምምነትና በመረዳዳት ላይ የተመሠረቱ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፋይዳ ካላቸው ማኅበራት ወይም ተቋማት አንዱ ደቦ ወይም ወንፈል ነው፡፡ ወንፈል ወይም ደቦ አገር በቀልና ነባር የኅብረት ሥራ ማኅበር ነው፡፡» ማለቱንም እዚህ መጥቀሱ ተገቢ ነው።

እንደ ተመለከትናቸው መረጃዎች ከሆነ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሰላምና ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚረዱ ማህበራዊ ድርጅቶችም ናቸው። በመሆኑም የእርሻ የኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረተሰቡን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥና ረሀብን ለማጥፋት በሚደረገው ጥረት የጎላ ድርሻ እንዳላቸው አሁን ዓለም ያመነ ይመስላል። [...] የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መወሰድ ካለባቸው እርምጃዎች መካከል በእርሻ የኅብረት ሥራ ማህበራትና በሌሎች የገጠር ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ የመዋዕለ ንዋይ ድጋፍ ማድረግ እንደሚያሻም ተመራማሪዎቹ ይመክራሉ። ከዚህ አኳያ ስንመለከተው ደቦም ሆነ

> **ደቦን ወንዶች መሬታቸውን ለማረስ፣ ለመዝራት፣ ቤት ለመሥራት፣ አጥር ለማጠር፣ ሰብል ለማረም .....፤ ሴቶች ጥጥ ለመፍተል፣ ቤት ሲሠራ ውኃ ለመቅዳት፣ የማኅበር፣ የሰንበቴ የሠርግ ድግስ ለመደገስ .... ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ጋር በመሆን ለስኬታማነት ይጠቀሙበታል**

ወንፈል ወይም ጂጊ፣ በተለይ ከግብርናው ዘርፍ ውጤታማነትና የአርሶ አደሩ ተጠቃሚነት አኳያ፣ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል ማለት ነው።

የዓለም የምግብ ፕሮግራም (FAO) 23ኛውን የዓለም የምግብ ቀን ሲያከብር መሪ ቃሉን «የእርሻ ኅብረት ሥራ ማህበራት ዓለምን የመመገቢያ ቁልፍ ዘዴዎች» (Agricultural Cooperatives key to feeding the world) የሚለውን ማድረጉም ያለ ምክንያት አይደለምና ደቦ በተለይ ለግብርናው ዘርፍ ወሳኝ ማህበራዊ እሴት ነው ማለት ነው።

ደቦን ወንዶች መሬታቸውን ለማረስ፣ ለመዝራት፣ ቤት ለመሥራት፣ አጥር ለማጠር፣ ሰብል ለማረም .....፤ ሴቶች ጥጥ ለመፍተል፣ ቤት ሲሠራ ውኃ ለመቅዳት፣ የማኅበር፣ የሰንበቴ የሠርግ ድግስ ለመደገስ .... ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው ጋር በመሆን ለስኬታማነት ይጠቀሙበታል፡፡

### ደቦ እንደ ተቋማት መጠሪያ፣ ማንነት መለያ

ከላይ የተመለከትነው የደቦ ትርጓሜና ፋይዳ በመሠረታዊነት የሚቀመጥ፤ በችግር ፈቺ ሚናውም የሚታይ ሲሆን፤ በሌሎች ዘርፎችም እየገባ ለሌላ ፋይዳ እንደሚውልም ታሳቢ ማድረጉ ተገቢ ነው። በመሆኑም፣ ይህ አምዳችን «አገርኛ» እንደ መሆኑ መጠን አገራዊ የሆኑ ነገሮችን ያበረታታልና ደቦ በሌሎች ዘርፎችም ውስጥ በመግባት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑን ሊያመለክት ይፈልጋል።

ዛሬ ዛሬ በአገራችን በአብዛኛው ለንግድም ሆነ ሌላ የሚሰጡ ስያሜዎች ዲቃላ ቢሆኑም፤ አልፎ አልፎም ቢሆን አገራዊ ስያሜን በመስጠት አገር በቀል ተቋማቱን ፍፁም አገር በቀል የማድረግ ሥራን እየሠሩ ያሉ ወገኖች አሉ። ይህ ደግሞ ሊያስመሰግናቸው የሚገባ ትልቅ ተግባርና እሴትን የማስቀጠል እንቅስቃሴ ነውና እዚህ ሊጠቀሱ የግድ ይሆናል።

መጠሪያቸውን፣ ልክ እንደዚህ ገጽ አምድ «አገርኛ» ያደረጉ ተቋማትም (አገር በቀል የሆኑ) እንደዚሁ ደቦን መለያቸው አድርገውት እንመለከታለን። ደቦን መጠሪያቸው ካደረጉት ተቋማት መካከል፤

«ደቦ» (ከደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ሥራዎች አንዱ)፤ «ደቦ» (የአማርኛ እትም መጽሐፍ በ60 ነባር እና አዳዲስ ጸሐፍት የተጻፈ - ስብስብ)፤ ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክስዮን ማኅበር፤ ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ፤ ደቦ የእርዳታ ማህበር፤ «ደቦ» (የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኮቪድ-19 በሽታ ስርጭትን ለመከላከል የሚያግዝ «ደቦ» የተሰኘ የሰዎች ንክኪ መለያ የአንድሮይድ ስልክ መተግበሪያ ይፋ ማድረጉን አስታወቀ። የሚለውን ዜና ያስታውሷል።)፤ ደቦ (ውቤ በረሀ አካባቢ ያለ ምግብ ቤት)፤ ደቦ መተግበርያ (የኢንተርኔት አፕ)፤ ደቦ ኢንጂነሪግን (Debo Engineering) (በኢትዮጵያ የእፅዋትን በሽታ በተንቀሳቃሽ ስልክ በመጠቀም መለየት የሚያስችል መተግበሪያ፣ በ4 ቋንቋዎች እና በድምጽ እገዛ የሠራ አገር በቀል ድርጅት) እና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ከዚህ የምንረዳው የ«ደቦ» ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ... ፋይዳዎች ቀላል አለመሆናቸውን ብቻ ሳይሆን ህብረት፣ አንድነት፣ መተጋገዝ፣ መተባበር ... ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ነው። (በነገራችን ላይ እንዲህ ዓይነት፣ ቱባ ባህላዊ እሴትን የሚያስተዋውቅ፣ ለትውልድ የሚያስተላልፍ፣ ወደ ፊት የሚያስቀጥል ... አስተሳሰብን መሠረት አድርገው ለድርጅታቸው፣ ለአካባቢዎቻቸውም ይሁን ተቋማት ስያሜን የሚሰጡ አካላትን ልናደንቅ፣ ልናመሰግናቸውም ይገባልና ሌሎችም የእነሱምን አርአያ ልንከተል ይገባል የሚል ማሳሰብያን ጣል ብናደርግ ከአምዳችን አኳያ ተገቢ ነው እንላለን።

### ደቦ/ጂጊን ከሃይማኖት አኳያ

ከላይ ከተቋማት ስያሜ አኳያ እንደተመለከትነው ሁሉ፣ ከሌሎች ማህበራዊ ዘርፎች አኳያም የሚኖረው ፋይዳና ሚና ቀላል እንደማይሆን መገመት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ ምክንያታችን የሚከተለው ነው።

ደቦ ማለት «ጂጊ» ነው ካልን ጂጊን በሃይማኖትም ተገቢውን ስፍራ ይዞ የምናገኘው ሲሆን፤ ለዚህም በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ያለውን ቁርአን አቀራር ሥርዓት፣ ማለትም «ጂጊ ቁርአን»ን (ቁርአን በተናጠል ሕብረት) መመልከት ይቻላል። (ለምሳሌ የበድሬ ሐሪማን «ሕብረት ቁርአን» መንዙማ ከዩቲዩብ በማውረድ መመልከት ይቻላል።)

(እዚህ ላይ የአንድ «ቃል»፣ ከዛም በዘለለ መልኩ የአንድ «ጽንሰ ሀሳብ» (እዚህ ጋ «ጂጊ»ን እንደ ቃል ሳይሆን እንደ ጽንሰ ሀሳብ መጠቀማችንን ልብ ይሏል) በተለያዩ አውዶችና ሰብአዊ አገልግሎቶች ውስጥ ሲገኝ የእነዛን ተቋማት የጋራ ማንነት የሚያመለክት መሆኑን በቅንፍ አስቀምጦ፣ ለሌላ ጥናት አመቻችቶ ማለፍ ተገቢ በመሆኑ አድርገነዋል።)

በአጠቃላይ፣ ደቦ እንደ አንድ ዘመናዊ የኅብረት ሥራ ማህበር ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። የኢኮኖሚያችን የጀርባ አጥንት (ግብርናው) ነውና ልንንከባከበው ይገባል። ከቱባ ማህበረ ባህላዊ እሴቶቻችን፣ ትውፊቶቻችን ... አንዱ ነውና ሳይበረዝና ሳይከለስ ለትውልድ ሊተላለፍ ይገባል። የስነልሳን ምሁሩ ፕሮፌሰር ባዬ ይማም «የእኛ የኢትዮጵያውያን አንድነት መገለጫዎች ሦስት ሲሆኑ እነሱም ስነ ልሳናዊ፣ ባህላዊና ስነልቦናዊ ናቸው» እንዳሉት ሁሉ፣ «ደቦ»ንና ሌሎችንም በተለያዩ ዘርፎች (ከላይ በሃይማኖትና ተቋማት ዘርፎች እንዳየነው ማለት ነው) በመመልከት የአንድነታችንን መሠረት ማጥበቅ ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ግብርናን በቴክኖሎጂ ለማሳለጥ የሚተጋ ወጣት

**አስናቀ ፀጋዬ**

የመጀመሪያ ዲግሪውን በቢዝነስ ማኔጅመነት ያገኘ ቢሆንም አባቱ የግብርና ምርምር ስራዎችን ይሰሩ ስለነበር በልጅነቱ ሲያነባቸው የነበሩ አብዛኞዎቹ መፅሃፍቶች ከግብርና ጋር የተያያዙ ነበሩ። ካደገም በኋላ በከፍተኛ ትምህርት ቆይታው ለማሟያ ይሰራቸው የነበሩ ፅሁፎች ግብርናን የሚዳስሱ ነበሩ።

ስራ የጀመረው በአዳማ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሲሆን በመምህርነት በቆየባቸው ጊዚያት በተለይ በማህበረሰብ ፕሮጀክቶች ላይ አንዳንድ ፅሁፎችን እንዲያዘጋጅና ችግሮችን ቀረብ ብሎ እንዲያይ እድል ፈጥሮለታል። ዛሬ ላይ ለሚሰራው ስራም ትልቅ መሰረት ጥሎለታል።

በአርሲ ዩኒቨርስቲ የቢዝነስ ትምህርት ቤት ሲመሰረትም በመምህርነት አገልግሏል። በዚሁ ዩኒቨርስቲ ቆይታው በግብርናው አካባቢ ማህበረሰቡን ቀረብ ብሎ ያለበትን ችግርና የትኛው ችግር ወደ ቢዝነስ ሊቀየር እንደሚችል ለመረዳት ችሏል።

በኢትዮጵያ የግብርና ስራ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን እንደ እድል ተጠቅሞ ስራ መስራት ይቻላል የሚል እምነት በውስጡ በማደሩ ከዛሬ ስምንት አመት በፊት ‹‹ለእርሻ›› የተሰኘና በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ነው የተባለለትን ለአርሶ አደሮች የዲጂታል ግብርና አገልግሎት የሚሰጥ ምህዳር (ፕላትፎርም) በመፍጠር ወደ ስራ ገባ።

በዚህም በርካታ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግና በዚሁ ምህዳር (ፕላትፎርም) ስር ላሉ ወጣቶች የስራ እድል መፍጠር አስቻለው። የግሪን አግሮ ሶሊዩሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መስራችና ማኔጂንግ ዳይሬክተር ወጣት አብርሃም እንድሪያስ።

ወጣት አብርሃም የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘው ከአዳማ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስ ማኔጅመንት ሲሆን የሁለተኛ ዲግሪውን ደግሞ በዚሁ የትምህርት መስክ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተቀብሏል። በተማረበት የትምህርት መስክም በአዳማና በአርሲ ዩኒቨርሲቲዎች በመምህርነት አገልግሏል።

በመምህርነት አገልግሎት ቆይታው በማህበረሰብ ፕሮጀክቶች ላይ አንዳንድ ፅሁፎችን እንዲያዘጋጅ ረድቶታል። ችግሮችን ቀረብ ብሎ እንዲያይም እድል ፈጥሮለታል። ከዚህ ባለፈ በግብርናው አካባቢ ማህረሰቡ ያለበትን ችግር በቅርበት ለማየት አስችሎታል። ከዚህ ችግር በመነሳት ቢዝነስ መፍጠር እንደሚቻልም ተረድቷል።

ከመምህርነት አገልግሎቱ በኋላ በግብርናው ዘርፈ ላይ በስፋት ሲሰራ መቆየቱና ስራን የማስፋት ፍላጎት በውስጡ መኖሩ ይህን ፕላትፎርም ለመፍጠር ምክንያት ሆኖታል። በተለይ ቀደም ሲል የግብርና ማሽነሪዎችን ለአርሶ አደሮች በሚያከራይበት ወቅት በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመሄድ እድሉ ነበረው። በዚህ ግዜም በጣም ሰፊ እድል እንዳለ ለማወቅ ችሏል። ነገር ግን ሁሉንም ፍላጎት አንድ ኩባንያ ብቻውን ሊያሟላ እንደማይችል ተረድቷል።

በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ግብርና ዝናብ ተኮርና ወቅትን ጠብቆ የሚከናወን በመሆኑ አንድ ስራ ብቻ በመስራት ውጤታማ የሆነ የግብርና አገልግሎት መስጠት እንደማይቻል ተገንዝቧል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች የመሬት ይዞት በጣም ትንሽ መሆኑን አውቋል። ከዚህ በመነሳትም እ.ኤ.አ በ2018 በዚህ ዘርፍ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ምን እንደሚመስል ኬኒያ፣ ናይጄሪያና ህንድ በመጓዝ የመጎብኘትና ተሞክሮውን የመቅሰም አጋጣሚው ነበረው።

በዚህም ሀገራቱ የግብርና አገልግሎታቸውን እንዴት ማሳደግ እንደቻሉና በጊዜው የዲጂታል ግብርና አገልግሎት በደምብ እየተለመደ የመጣበት መሆኑን በሚገባ ለመረዳት ችሏል። በኢትዮጵያ ግን በርካታ አርሶ አደሮች ጋር ለመድረስ በተለይ ያለው የግብርና ማሽነሪ አነስተኛ በመሆኑ ይህን ቢዝነስ በተለመደው መንገድ ለማሳደግ እጅግ አስቸጋሪ እንደነበርም አውቋል።

ይሁንና የግብርና አገልግሎቱን ዲጂታል ማድረግ ቢቻል የግብርና ማሽነሪዎች ያላቸውንና ሌሎች የግብርና ግብአቶችን የሚሸጡ ሰዎችን በማሳተፍ




ፎቶ፡- በአስናቀ ፀጋዬ

**ወጣት አብርሃም እንድሪያስ፤**

በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ከድምዳሜ ላይ ደረሰ። በዚሁ መነሻነትም ‹‹ለእርሻ›› የተሰኘ የዲጂታል ግብርና አገልግሎት ፕላትፎርም ፈጠረ።

በግዜው ፕላትፎርሙ ስራ ላይ መዋል እንደጀመረ አንዱና ትልቁ ችግር በገጠር አካባቢ የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ አለመኖር ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የአርሶ አደሮች የማንበብና የመፃፍ ክህሎት አናሳ መሆን ፕላትፎርሙ በሚፈለገው ልክ ስራ ላይ እንዳይውልና አርሶ አደሩን በቀጥታ ለማግኘት ችግር ፈጥሯል።

አርሶ አደሮች ያላቸው ስልክ ‹‹አንድሮይድ›› አለመሆንም ሌላኛው ችግር ነበር። ከዚህ ባለፈ ደግሞ አዲስ ቴክኖሎጂን ለመቀበል ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆንም ተጨማሪ ችግር ፈጥሯል። የግብርናው ዘርፍ እንደሌሎቹ ዘርፎች በግለሰብ ደረጃ በቀላሉ ተገብቶበት የሚሰራበት አለመሆኑና ከሌሎች መንግስታዊና የምርምር ተቋማት ጋር በመሆን የሚሰራበት መሆኑም ሌላኛው ችግር ነበር።

ከነዚህ ችግሮች በመነሳት በአራት ክልሎች ማለትም በኦሮሚያ ሳቡሬ፣ በሶማሌ ጅጅጋ፣ በአማራ ባህርዳርና በሲዳማ ሃዋሳ ላይ ቢሮ እንዲቋቋም ተደረገ። በነዚሁ ቢሮዎች አማካኝነትና አዲስ አበባ ላይ ባለው ቢሮ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በቀጥታ አርሶ አደሩን አግኝተው ይነጋገራሉ ። ይህም ችግሩን ከምንጩ ለመረዳት አስችሏል።

በችግር ውስጥ ለመስራትም ጥረት ተደርጓል። በሌላ በኩል ደግሞ አርሶ አደሩ ማንበብ መፃፍ፣ የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) እውቀት ችግር ስላሉበትና አገልግሎቱን በቀጥታ ሊጠቀም የማይችል በመሆኑ የሞባይል መተግበሪያና የጥሪ ማእከል ከመገንባት ባለፈ ‹‹ለእርሻ ኤጀንት›› የሚባሉ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ስራ የሌላቸው ወጣቶችን በማሰልጠን የሞባይል መተግበሪያውን በመጠቀም በአርሶ አደሩና በፕላትፎርሙ በኩል ድልድይ ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። እስካሁንም 642 የሚሆኑ ወኪሎች (ኤጀንቶች) ሰልጥነው ስራውን እያከናወኑ ይገኛሉ።

አጋርነት መገንባት ግዜ የሚፈጅ ጉዳይ መሆኑን በማጤን በአጋርነት ከድርጅቱ አቅም በላይ የሆኑ ነገሮችን ለአብነትም አርሶ አደሮችን የማሰልጠን ስራዎችን እንዲያግዙ፣ ወጪዎችን እንዲያጋሩና እነርሱ ጋር ያለውን እውቀት እንዲያካፍሉ በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት ተሞክሯል።

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች አነስተኛ ማሳ ያላቸው በመሆኑ ግብርናቸውን ለማከናወን የተለያዩ አገልግሎቶችን ይፈልጋሉ። በተለይ ደግሞ ለወጣቱ ግብርና ከባድ ነው። መሬት ኖሯቸው የግብርና ማሽነሪዎችን ለማግኘትም ይቸገራሉ። መሬታቸውን ካረሱ በኋላም ምርጥ ዘር፣ ማደበሪያና ሌሎች ግብርና ግብዓቶችን በቀላሉ ማግኘት አይችሉም። ከግብርና ጋር የተያያዙ ምክሮችንም እንደልብ አያገኙም። ይህ ምህዳር (ፕላትፎርም) የተዘጋጀውም በቴክኖሎጂ በተደገፈ መልኩ የግብርና ስራውን ለማቅለል ነው።

ይህንን ለማድረግም የሞባይል መተግበሪያ፣ የጥሪ ማእከልና ለእርሻ ኤጀንት የሚባል ሞዴል ተገንብቷል። በዚህ ሞዴል አማካኝነት የእርሻ ኤጀንቶችን እንደ ድልድይ በመጠቀም ለአርሶ አደሩ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ አግሮ ኬሚካልና ሌሎች የግብርና ግብአቶች ይቀርባሉ።

ለእርሻ ኤጀንቶች አርሶ አደሩን ፍላጎት እየሰበሰቡ በአቅራቢያው ካሉ የግብርና ግብአት ሱቆች ጋር ያገናኛሉ። በአቅራቢው ካሉ የግብርና ማሽነሪ ባለቤቶች ጋርም ያገናኙታል። አርሶ አደሩ የተሻለ ውሳኔ እንዲወስን የአየር ንብረትና የማዳበሪያ መረጃዎችንና ሌሎች የተለያዩ ምክሮችን ያቀርባሉ።

ይህም አርሶ አደሩ ጉልበት ሳያወጣና ግዜ ሳያጠፋ እነዚህን የግብርና ግባአቶች በቀላሉና በፈለገው ግዜ እንዲያገኝ አስችሎታል። የግብርና ማሽነሪዎችንም ብዙ ሳይለፋ እንዲያገኝና የአየር ንብረት መረጃዎችንና ሌሎች የግብርና ምክሮችን ለማግኘት ረድቶታል።

በአሁኑ ግዜም በአራት ክልሎች ላይ በዚሁ ፕላትፎርም አማካኝነት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። በዚሁ ዲጂታል ፕላትፎርም አማካኝነትም 71 ሺ የሚሆኑ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል። ከ 642 በላይ ለእርሻ ኤጀንቶችም አሉ። ከ172 በላይ የትራክተርና ኮምባይነር ባለቤቶች በዚህ ፕላትፎርም ውስጥ ተካተው ለአርሶ አደሩ አገልግሎት ይሰጣሉ። 29 የሚሆኑ ደግሞ ግብአት የሚሸጡ የግብርና አገልግሎት ማእከላት በፕላትፎርሙ ውስጥ ተካተዋል። ከ3 ሺ 100 በላይ የመንግስት የግብርና ኤክስቴንሽን ኤጀንቶች ከዚህ ፕላትፎርም የምክር አገልግሎት ያገኛሉ።

በሂደት ደግሞ የአየር ንብረት ምክር አገልግሎት ለአርሶ አደሩ ሲሰጥ ምክሩን ተከትሎ አርሶ አደሩ በዝናብ መብዛት ወይም ማጠር ምክንያት ‹‹ሰብሌ ቢጎዳ ምንድን ነው የማደርገው?›› የሚል ጥያቄ ሲመጣ በዘንድሮው አመት ከኦሮሚያ ኢንሹራንስ ጋር በመሆን በአራት ወረዳዎች ላይ 129 የግብርና ኢንሹራንስ ፖሊሲ በሙከራ ደረጃ ተጀምሯል።

በአሁኑ ግዜ በግሪን አግሮ ሶሊዩሽን ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለ51 ሰራተኞች የስራ እድል የፈጠረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ሃያ አራቱ ለእርሻ ፕላትፎርም ላይ ይሰራሉ። በፕላትፎርሙና በአርሶ አደሮች መካከል ድልድይ ሆነው ለሚያሳልጡ 642 የለእርሻ ኤጀንቶች ወጣቶችም የስራ እድል ተፈጥሯል። የግብርና ግብአቶችን ከሱቆች ለአርሶ አደሩ ለሚያደርሱ ከ80 በላይ ለሚሆኑ የሞተር ሳይክል ባለቤቶችም ተመሳሳይ የስራ እድል ተፈጥሯል።

ግሪን አግሮ ሶሊዩሽን በለእርሻ ዲጂታል ፕላትፎርም በመጪዎቹ ሁለት አመታት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰራቸውን ስራዎች አጠናክሮ ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የመሆን እቅድ አለው። ቴክኖሎጂውን በማጠናከር የሚያስለጥናቸውን የኤጀንት ቁጥሮች በመጨመር አሁን ላይ ያለውን የአማርኛ ፣ ኦሮሚኛ ፣ ሲዳሚኛና ሶማሊኛ ቋንቋ በማሳደግ ለመላው ኢትዮጵያ አገልግሎቱ የሚዳረስበትን መንገድ ለማመቻቸትም ውጥን ይዟል።

በእንዲህ አይነት ዲጂታል ፕላትፎርሞች አፍሪካ ውስጥ ያሉ አርሶ አደሮች ያሉባቸው ችግሮች ተቀራራቢ በመሆናቸው ኬኒያ፣ዛምቢያና ኮትዲቯር የገበያ እድሎችን ለማጥናት ሙከራ እየተደረገ ይገኛል። ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ድርጅቶችና መንግስታዊ ተቋማት ጋርም አጋርነት የማጠናከር ሃሳብም አለ።

‹‹የድርጅቱ ዋነኛ አላማ በ2025 እ.ኤ.አ 4 ሺ 500 ለእርሻ ኤጀንቶች መድረስ ነው›› የሚለው ወጣት አብርሃም፤ አንድ ኤጀንት በአመት እስከ 1 ሺ አርሶ አደር ይደርሳል ተብሎ እንደሚታሰብ ይናገራል። ይህም ለ4 ነጥብ 8 ሚሊዮን አርሶ አደር አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያችልና በዚሁ አቅጣጫ መሰረት ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም ይጠቁሟል። የኤጀንቶቹ ቁጥር በመጨሩ በተለይ በገጠር አካባቢ ለወጣቶች የሚፈጠረው የስራ እድል የዚያኑ ያህል እንደሚጨምርም ያደርጋል።

አርሶ አደሩ የግብርና ግብአቶችን ለማግኘት ግዜውንና ጉልበቱን እንደሚያባክን ፤ ገንዘብም እንደሚያወጣ የሚናገረው ወጣት አብርሃም፤ በዚህ ፕላትፎርም አርሶ አደሮች ወደከተማ መምጣት ሳይጠበቅባቸው ግብአቶችን በለእርሻ ኤጀንቶች አማካኝነት በአቅራቢያቸው ለማግኘት እንደሚያስችላቸው ይጠቁማል። ይህም የሚያወጡትን ግዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ እንደሚቆጥብላቸው ይገልፃል።

አርሶ አደሮቹ በነዚህ ኤጀንቶች አማካኝነት አገልግሎቱን ሲያገኙ 5 ከመቶ ኮሚሽን እንደሚከፍሉና ከዚህ በፊት ከሚያወጡት ወጪ ባነሰ አገልግሎቱን ለማግኘት እንደሚያስችላቸውም ነው ወጣት ቢኒያም የሚገልፀው። ከአርሶ አደሮቹ ላይ የሚሰበሰበው ኮሚሽን ለድርጅቱና ኤጀንቶቹ ገቢ እንደሚሆንም ያመለክታል። እስካሁን ፕላትፎርሙ ገቢ እያመጣ ቢሆንም ወጪውን ግን ሙሉ በሙሉ መሸፈን እንዳልቻለም ነው የሚናገረው።

ቴክኖሎጂ መሳሪያ እንጂ በራሱ አገልግሎት ሊሆን የማይችል በመሆኑ በተለይ ደግሞ ለአርሶ አደሩ ቴክኖሎጂ ለመሸጥ ቢሞከር ቴክኖሎጂውን ሳይሆን በቴክኖሎጂ በኩል የሚያገኘውን አገልግሎት እንደሚፈልግ ነው ወጣት አብርሃም የሚጠቁመው። ከዚህ አኳያ ይህን ለማድረግ የቴክኖሎጂ ውጤቶችንና አሰራሮችን የሚያውቁ በርካታ ወጣቶች በመኖራቸው ወደገጠር ወርደው አርሶ አደሩን በመቅረብ ውይይት ቢያደርጉ በግብርናው በኩል ያለውን ችግር በቴክኖሎጂ መፍታት እንደሚቻል ያመለክታል።

ከዚህ ባለፈ በግብርናው አካባቢ ተለማማጅ ሆነው ቢሰሩ፣ ወደ ግብርና ሚኒስቴር በመሄድ በቴክኖሎጂ ረገድ ምን አይነት እገዛ እንደሚያድርጉ ቢጠይቁና የአንድና የሁለት ወር የስራ ልምምድ ቢሰሩ፣ ግብርናን በተመለከተ መረጃ ቢያገኙ ብሎም መሬት ላይ ካለው አውድ ጋር ቢገናኙ ግብርና ላይ ብዙ ተአምር መስራት እንደሚቻልም ይጠቁማል።

ወደእነርሱ ድርጅት ወጣቶች ሲመጡ የመጡበትን ልምድና ያላቸውን እውቀት እንደሚያካፍሏቸውና ልምምድ ሲፈልጉም ትምህርት እንደሚሰጣቸው ነው ወጣት አብርሃም የሚያመለክተው። ወጣቶቹ ከሚፈልጉት ነገር ጋር አብሮ የሚሰራ ድርጅቱ የሚያውቀው አጋር ካለ ወደ እርሱ እንደሚላኩም ይናገራል።

በመሆኑም ራሳቸው አካባቢ ቁጭ ብለው እድል እንዲመጣ ከመጠበቅ በጥቂቱ ቴክኖሎጂ ላይ የሚሰሩት ነገር ካለ ወደፊት መጥተው ከድርጅቶች ጋር መነጋገር ቢችሉና በተለይ ገጠር አካባቢ ሄደው ገበሬውን ህይወቱን ቢያዩና የትኛው ነገር ዲጂታላይዝ መሆን ይችላል የሚለውን ቢረዱ በግብርናው ዘርፍ ውጤታማ ስራ መስራት እንደሚያስችላቸው ይመክራል።

# የማዕድን ዘርፉን ለማነቃቃት ያለመ ኤክስፖ

**ስምስም መንግሥቱ**

ዓለምአቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ሊካሄድ በጣት የሚቆጠሩ ቀናቶች ብቻ ቀርተውታል። ኤክስፖውም አምራችና ገዥን ጨምሮ በዘርፉ ኢንቨስት የሚያደርጉ፣በገንዘብ፣በሀሳብ፣በእውቀትና በቴክኖሎጂ እገዛ ለማድረግ ፍላጎት ያላቸው፣በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ባለድርሻ አካላት የሚያሳትፍ ነው። ዛሬም ድረስ ዓለም አቀፍ ስጋት በሆነው የኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ፣እንዲሁም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ላለፉት ሁለት አመታት በተካሄደው ጦርነትና በሌሎችም ምክንያቶች የማዕድን ዘርፉ ተቀዛቅዞ መቆየቱ ይታወቃል።

በአሁን ወቅትም ከማምረት እስከ ገበያ ባለው ሰንሰለት ውስጥ ተቀዛቅዞ የነበረውን የማዕድን ዘርፍ ማነቃቃት ያስችላል የተባለው ኤክስፖ ሊጀመር ቀናቶች ቀርተውታል። በኢትዮጵያ አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚካሄደው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ በዘርፉ ልማትና ቴክኖሎጂ ተሞክሮ ያላቸው የውጭ ኩባንያዎችና የሀገር ውስጥ የዘርፉ አምራች ኢንደስትሪዎችን በማገናኘት በሚኖረው ሚናም ትልቅ አቅም ይፈጠራል የሚል እምነትም አሳድሯል።

በህዳር ወር መጀመሪያ ላይ በሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል ተብሎ ስለሚጠበቀው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ በተመለከተ የማዕድን ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ፌቨን ተሾመ እንዳስረዱት፤የማዕድን ቴክኖሎጂ ኤክስፖው በዘርፉ ላይ የሚገኙትን ኩባንያዎች እርስበርስ በማስተዋወቅ የገበያ ትስስርና የቴክኖሎጂ የልምድ ልውውጥ እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣እንደ ባንክ ያሉ የፋይናንስ ተቋማትንም በማሳተፍ ተቋማቱ ዘርፉን በገንዘብ በመደገፍ አበርክቶ እንዲኖራቸውም ዓላማ ያደረገ ነው። የሀገር ውስጥና የዓለምአቀፍ የዘርፉን ኩባንያዎችና የፋይናንስ ተቋማት በጋራ በማሳተፍ ዘርፉን በማነቃቃት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብንም ታሳቢ ያደረገ ጭምር ነው።

በተለይም ዓለም አቀፍ የዘርፉ ኩባንያዎች የማዕድን ቴክኖሎጂ በማስተዋወቅ በኩል የሚኖራቸው ሚና ከፍ ያለ በመሆኑ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንደስትሪዎች ልምድና ተሞክሮ እንዲያገኙ ሚኒስቴር መስሪያቤቱ በማዕድን ዘርፍ ለተሰማሩ ዓልምአቀፍ ኩባንያዎች፣ለማዕድን ዘርፉ የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብና በመጠቀም ልምዱ ያላቸውን በኤምባሲዎች አማካኝነት አስቀድሞ ጥሪ አድርጓል። ጥሪው ከተደረገላቸው መካከልም ጣሊያን፣አውስትራሊያ፣ፈረሳይ፣ከአፍሪካ ሀገራትም የዘርፉ ባለድርሻዎች ጥቂቶቹ ሲሆኑ፣ጥሪው የደረሳቸው አብዛኞቹ አገራትም ፍላጎታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ በዓለም ገበያ ላይ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የማዕድን ሀብቶች ቢኖሩም፣በተለያየ ምክንያት የገበያ ዕድል ያልተፈጠረላቸው መኖራቸውንና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጉዳይ እንደሆነ ያስታወሱት ዳይሬክተሯ፤የማዕድን ቴክኖሎጂ ኤክስፖው እንዲህ ላሉ ክፍተቶች መፍትሄ እንደሚሆን ይጠበቃል ብለዋል።

እንደርሳቸው ገለጻ፤ ለሶስት ቀናት ክፍት ሆኖ ከሚቆየው ኤክስፖ ከጉብኝት ባለፈ በተለይም ጊዜንና ጉልበትን በሚጠይቅ አድካሚ ሁኔታ በየእለቱ የሚንቀሳቀሱ ባህላዊ የማዕድን አልሚዎች ወይም አምራቾችን ድካም የሚያቃልል፣እንዲሁም በባህላዊ መንገድ ሲያለሙ የሚባክነውን ማዕድን ለማስቀረትና በጥራት መጓደልም የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታት የሚረዳቸው ጠቃሚ ነገር እንደሚያገኙ ይጠበቃል።

ሁሉንአቀፍናአሳታፊየሆነዓለምአቀፍኤክስፖማካሄድ የተለመደ መሆኑን ያስታወሱት ዳይሬክተሯ፤ኢትዮጵያም በማዕድን ዘርፍ ኤክስፖ በማዘጋጀት አንዷ ሀገር ለመሆንና ለቀጣይ መሠረት ለመጣልም እንደጅማሬ የሚወሰድ መሆኑን አመልክተዋል። ከኤክስፖው እንደሀገር ስለሚጠበቀው ውጤትም እንደገለጹት፤የሀገር ውስጥ የዘርፉ አምራች ኢንደስትሪዎችና ላኪዎች በዓለምአቀፍ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው፣ተወዳዳሪ ሆኖ ገበያውን ሰብሮ ለመግባት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር የሌሎችን ተሞክሮ እንዲያገኙ፣በተለይ ደግሞ ባህላዊ የማዕድን አምራቾች ያለባቸው የገንዘብ አቅም እንዲፈታላቸው ከባንኮች ጋር ትስስር የሚፈጥሩበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው፣የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከሚጠበቀው ውጤት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። በዓለምአቀፉ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ እምቅ የሆነ የማዕድን ሀብት እንዳላት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከማስቻሉ በተጨማሪ የዘርፉ ኩባንያዎች ፊታቸውን ወደ ኢትዮጵያ እንዲያዞሩም ያግዛል።




የማዕድን ዘርፉን ለማነቃቃት፤

ኤክስፖውን የሚያዘጋጀው ማዕድን ሚኒስቴር ተባባሪ ከሆኑት ተቋማት ጋር የውል ስምምነት በመፈራረም ዝግጅቱን የተሳካ እንዲሆን ጥረት እያደረገ ሲሆን፣በዚህ ረገድም የኢትዮጵያ አየርመንገድ ይጠቀሳል። አየርመንገዱ ከውጭ ለሚገቡ የኤክስፖ ተሳታፊዎች በመጓጓዣ እና በሆቴል አገልግሎት ላይ በሚሰብ የዋጋ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ አጋዥ ሆኖ ይሰራል። የኢትዮጵያን የማዕድን ፖሊሲ በማስተዋወቅና በዘርፉ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የውጭ ኩባንያዎችም በሀገሪቱ ያሉ የኢንቨስትመንት አማራጮችን ለማየትም ዕድል ይሰጣል። የማዕድን ቴክኖሎጂ ኤክስፖው በተዘዋዋሪ የቱሪዝም ኢንደስትሪው ገቢ ላይ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል። ከዚህ አኳያ ኤክስፖው ዘርፈብዙ ጥቅሞች ይገኙበታል ተብሎ ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ውስጥ ጉልህ ሚና ይወጣሉ ተብለው ከተለዩት ዘርፎች አንዱ የሆነው ይህ የማዕድን ዘርፍ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲወጣ ለማስቻል በመንግሥት በኩል እየተደረገ ስላለው እንቅስቃሴ፣በሀገር ውስጥ የኤክስፖው መዘጋጀት ስለሚኖረው ፋይዳና በኤክስፖው የሚፈጠረውን አጋጣሚም በመጠቀም ረገድ በዘርፉ ላይ የሚገኙትን በተለይም በላኪነት ሥራ ላይ ከተሰማሩ መካከል አንዳንዶችን ጠይቀን ሀሳባቸውን አካፍለውናል። በቅድሚያም ሀሳባቸውን ያካፈሉን የኤ ዋይ ኤስ ኤስ ፕሪሽስ ስቶን ኤንድ ጂውለሪ ኤክስፖርተር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ባለቤት አቶ ዓለምነህ የሻነህ ናቸው።

አቶ ዓለምነህ ኩባንያቸው ከኤክስፖው ምን እንደሚጠብቅና አገኛለሁ ስለሚለው ጥቅም ላቀረብንላቸው ጥያቄ‹‹የኤክስፖው አስፈላጊነት ወይንም ጥቅሙ የሚያጠያይቅ አይሆንም። ላኪ የሚለው ስያሜ በራሱ ገበያ ፈላጊ ማለት ነው። ለላኪውም ሆነ ለሀገር ጠቀም ያለ ገቢ የሚገኘው የውጭ ገበያ ሲገኝ ነው። በተለይ ደግሞ ኤክስፖው በሀገር ውስጥ መዘጋጀቱ ተጠቃሚነቱ የበለጠ ነው የሚሆነው። ላኪው ወጭ ሳያወጣና በብዙ ድካም ውስጥ ሳያልፍ ገዥዎች ያለበት ድረስ መጥተው ይገዙታል። ደንበኞችንም ለማፍራት እድል ያገኛል። ይሄ ትልቅ ጥቅም ነው። » በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። እንደ አቶ ዓለምነህ፤ እስካሁን ባላቸው ተሞክሮ የኢትዮጵያ ማዕድን በብዙ የዓለም ሀገራት ተፈላጊ ነው። የኤክስፖው መዘጋጀት እነርሱንም ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል። ብዙዎችም ይመጣሉ። ለአብነትም የኢትዮጵያን የኦፓል ማዕድን በብዛት በመግዛት ህንዶች ቀዳሚ ናቸው። እርሳቸውም ከህንድ ጋር ባላቸው የገበያ ግንኙነትና በተለያዩ ሀገራት በሚካሄዱ ኤክስፖዎች ላይ ባገኙት የመሳተፍ አጋጣሚ የህንድ የማዕድን ነጋዴዎች ከኢትዮጵያ የገዙትን የኦፓል ማዕድን ገበያ ላይ ሲያቀርቡ ለደንበኛቸው ማዕድኑ የኢትዮጵያ እንደሆ ነው የሚገልጹት። ደንበኞቻቸው ፈልገው ከእነርሱ መግዛታቸው በተዘዋዋሪ የኢትዮጵያ ማዕድን በተለይም ኦፓል ተፈላጊ እንደሆነ ማሳያ ነው። በማዕድን ሀብቱ ባለቤቶች በሆኑት ኢትዮጵያውያን ሲቀርብላቸው ደግሞ ገዥዎች የበለጠ ይደሰታሉ የሚል እምነት አላቸው። ግብይቱ ከሁለተኛ ወገን ከሚሆን ቀጥታ መሆኑንም ይፈልጉታል። ደንበኛም በመያዝ ቋሚ ተጠቃሚ ለመሆን ያስችላቸዋል። ኤክስፖው በሀገር ውስጥ መዘጋጀቱ እንዲህ ያለ ጥቅምም እንዳለው ነው የተናገሩት።

የማዕድንና የቴክኖሎጂ ኤክስፖው የተወጣለት ስለመሆኑ ከወዲሁ መናገር ባይቻልም እየተደረገ ያለው ቅድመዝግጅትና የያዛቸው ዓላማዎች ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል ግምት የሚያሳድር መሆኑን መነሻ በማድረግ አቶ ዓለምነህን ጠይቀናቸው፡፡ እሳቸውም በማዕድን የላኪነት የሥራ ዘርፍ ላይ በቆዩበት ጊዜያቶች በኢትዮጵያ በተለያየ ጊዜ የማዕድን ኤግዚቢሽኖች እንደተካሄዱ ከመገለጹ ውጭ አላጋጠማቸውም። መኖሩን ቢያውቁ ኖሮ ግን ይሳተፉ እንደነበር ነው ያስታወሱት። ‹‹እንኳንም በሀገሬ ላይ ተዘጋጅቶ፣ በዶላር ከፍዬ በሌላ ሀገር ተሳትፌያለሁ። ከዚህ ቀደም በሀገር ውስጥ አላጋጠመኝም›› በማለት አብራርተዋል። የአሁኑ ግን ኤክስፖ የመጀመሪያቸው ነው። ከዝግጅቱም ለኩባንያቸውም ሆነ ለሀገር የሚጠቅም ትልቅ ውጤት ይገኛል የሚል ተስፋ አድርገዋል።

ሮዳስ የከበሩ ድንጋዮች ጌጦችና ቅርጾች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ባለቤት አቶ ሄኖክ ግርማ ግን ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የማዕድን ኤግዚቢሽኖች መዘጋጀታቸውንና እርሳቸውም መሳተፋቸውን ነግረውናል። በዘርፉ በላኪነትና በአምራችነት የካበተ ልምድ ያላቸው የውጭ ወይም ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን እንዲሁም ቴክኖሎጂን ባካተተ ያሳተፈ እንዳልነበር ነው የገለጹት። አቶ ሄኖክ እንዳሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የማዕድን ሀብት ብቻ ሳይሆን የማዕድንን ጥቅምና ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ግንዛቤ አልተፈጠረም የሚል እምነት አላቸው። የማዕደን ጌጣጌጥን አክብረውና ፈልገው የሚጠቀሙት ጥቂት ናቸው። ከሀገር ውስጥ ይልቅ




ኦፓል በኢትዮጵያ ከሚገኙ ዋና ዋና የማዕድን አይነቶች፤

የውጭ ማህበረሰብ የተሻለ ግንዛቤ ስላለው የዋጋውንም ውድነት ይረዳሉ። የማዕድን ቴክኖሎጂን ለማዘጋጀት እየተደረገ ካለው እንቅስቃሴ በይዘቱም ሆነ በተሰጠው ትኩረት ጥሩ ነገር ይጠብቃሉ። ኤክስፖው ስለማዕድን ጥሩ ግንዛቤ ያላቸውንና በዘርፉ ላይ የሚሰሩትንም የሚያሳትፍ በመሆኑ በሀገር ውስጥ የሚገኘውን አምራችና ላኪ በማነቃቃት እንዲሁም ማህበረሰቡ የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ከማድረጉ በተጨማሪ የዘርፉን የገበያ ችግር በመቅረፍ ረገድ ያለውን ፋይዳ የጎላ ያደርገዋል። የዓለም አቀፍ ገበያው ከማዕድን ዘርፎች በዋናነት የሚጠቀሱት እንደ ኦፓል፣ኤመራልድ፣ሳፋየር የመሳሰሉ የኢትዮጵያን የማዕድን አይነቶች በተዘዋዋሪ ከሌሎች ነጋዴዎች ከሚገበዩ ከመገኛው ሀገር መግዛት መቻላቸው አመኔታቸውን ከፍ ያደርግላቸዋል። ‹‹ኢትዮጵያም ብራንድ ለመሆን ያስችላታል›› ብለዋል።

እንደ አንድ የማዕድን ላኪ ከኤክስፖው ምን ይጠብቃሉ ብለን ላቀረብንላቸው ጥያቄ አቶ ሄኖክ ጥሩ የሆነ ግብይት እንደሚኖር፣በገበያም ሆነ ስለማዕድኑ አይነት አዲስ እይታ እንደሚጠብቁ ነው ምላሽ የሰጡት። ‹‹ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ለማንሳት አውስትራላውያን ያገኙትን ብላክ ኦፓል እራሳቸው በዓለም ላይ በሚያዘጋጁት ኤክስፖ ላይ በማቅረብ የሀገሪቱ ባለሀብቶች በጨረታ በውድ ዋጋ መልሰው እንዲገዙት ያደርጋሉ። ከራሳቸው ምድር የተገኘውን በራሳቸው ዜጋ በውድ ዋጋ እንዲሸጥ በማድረግ ማዕድኑ ከፍተኛ ዋጋና ትኩረት እንዲኖረው ያደርጋሉ። እንዲህ አይነት ነገር አስፈላጊ ነው ብዬ አምናለሁ። እኛ ቀጥታ መሸጥ እየቻልን የሌላው ሀገር ነጋዴ ከእኛ ገዝቶ ለገበያ ማቅረብ የለበትም። እኛም በቀጥታ መሳተፋችን አዲስ የዋጋ እይታ እንዲኖረን ያስችለናል›› በማለት አስረድተዋል።

አቶ ሄኖክ ኤክስፖው ሁሉንም ማሳተፍ እንዳለበት ያምናሉ። ስለአስፈላጊነቱም አብነትን በመጥቀስ እንዳስረዱት አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ ማዕድኑን ሲገዛ ሻጩ ከየት እንደሆነ ያረጋግጣል። ይሄን የሚያደርገው የሚገዛው ማዕድን ከኢትዮጵያ ከሆነና ሻጩም ኢትዮጵያዊ ከሆነ ማዕድኑን በቁፋሮ ከመሬት የሚያወጣው አልሚም ይጠቀማል የሚል እምነት ስላለው ነው። ከአልሚው ጀምሮ ሁሉም በየደረጃው ተጠቃሚ መሆን ካልቻለ ከዚህ ቀደም እንደሚባለው የደከመው ሳይሆን ሳይደክም ጥቅም ለማግኘት የሚሯሯጠው ብቻ ተጠቃሚ ይሆናል። ይሄ ደግሞ በዘርፉ የሚነሳውን ቅሬታ ለመቅረፍም አያስችልም። ፍትሐዊነትንም አያረጋግጥም። በተለይ ደግሞ የባህል አልሚውንና ሳይንሳዊ የሆነ የገበያ እይታ የሌለውን ተጎጂ ያደርጋል። አምራቹን፣አዘዋዋሪውን፣ላኪውን፣ቀራጩን፣በአጠቃላይ የዘርፉን ተዋናይ የያዘ ኤክስፖ ሲሆን ውጤቱም ያማረ እንደሚሆንና በኢትዮጵያ በዘርፉ ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ በዘርፉ ያለው ሁሉ ተጠቃሚነቱና ተሳትፎው እኩል መሆን አለበት ይላሉ።

በተለያዩ ሀገራት በሚዘጋጁ የማዕድን ኤክስፖዎች ላይ የመሳተፍ እድል ማግኘታቸውን የገለጹልን አቶ ሄኖክ፤በኢትዮጵያ የሚዘጋጀው በተደጋጋሚ ኤክስፖ የማዘጋጀት ልምዱና ተሞክሮ ካላቸው ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆን ባይጠብቁም በሀገር ደረጃ ከዚህ ቀደም ያልተለመደ ነገር ለማምጣት ጥረት መደረጉ በራሱ ትልቅ ለውጥና ሊበረታታ እንደሚገባ ነው ያስረዱት። ይህ መሆኑ በራሱ የሚጨምረው እሴት መኖሩን ነው የገለጹት።

እንግዲህ ከአስተያየት ሰጪዎቹም ሆነ ከማዕድን ሚኒስቴር መረዳት የሚቻለው ኤክስፖው ትኩረት የተሰጠውና ትልቅ ውጤትም የሚጠበቅበት ነው። ውጤቱንም በጋራ እንጠብቃለን።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ደስ የሚል ደስታ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

የነፍሴ ራቁት ሴትነቷን ለብሷል..ሀሳቤ ጀምሮ የሚያበቃው እሷ ጋ ነው። እሷን ሳስብ ባልሞት እላለው፣ ለዝንታለም ብኖር እላለው፣ ደጋግሜ ብፈጠር እላለው። እሷን ሳስብ..ሀሳብ ይጠፋኛል..ጥበብ ይርቀኛል..ደግሞም ሀሳብ ይሞላኛል..ጥበብ ይወረኛል።

እሷን ሳስብ..ለብቻዬ እስቃለው..አፌ ውስጥ ሞልቶ የሚፈስ የምስጋና መዐት ይፈጠራል። እሷን ሳስብ እንደ እስቅያስ፣ እንደ ሙሴ፣ እንደ አብረሀም፣ እንደ ሰለሞን፣ እንደ ኤሊያስ ሀይል ይጎበኘኛል። እሷን ሳስብ ደስ የሚል ደስታ ደስ ይለኛል።

እሷን ሳስብ ከምድር ወደ ሰማይ በተዘረጋ የወርቅ መሰላል ላይ እመላለሳለው። በእግዜር ታቅፌ፣ በእየሱስ ተስሜ..እሳታማ መንበሩን ነክቼ ሰው እሆናለው። ነፍሴ ማረፊያ ታጣለች..እዛም ልሂድ እዚም ልርገጥ በብኩርና ፊት ነኝ..እሷን ሳስብ ምድር ሁሉ መንገዴ ናት።

እሷን ሳስብ ብዙ ነኝ። እልፍ መዐት። ከዚህ እስከዛ ጥግ የሌለኝ። አለም ምድር የማትበቃኝ..አድማስ ጠረፍ የጠበበኝ። እሷን ሳስብ ከዋክብታማ ሰማይ ነኝ..በብርሀን የሚያበራ፣ በጨለማ የደመቀ ጸደያማ ቀለማት። ሳቅ ያረበበት፣ ፈገግታ የተዋበበት ነፍስና ስጋ።

ፈንጥገዬ ተኝቼ ፈንጥገዬ እነቃለው..ከንጋት መልስ ህይወቴ ውስጥ እሷ እንዳለች ሳስብ በራሴ ውስጥ ሌላ እሆናለው። ፈንጥዞ ተኝቶ ፈንጥዞ መንቃት ምን እንደሚመስል በእሷ ነው ያየሁት..በነፍሴ አለላ።

እያደርኩ አዲስ ነኝ..እየከረምኩም ሌላ። እሷ ጋ እስከደርስ ቅርቤ ሩቅ ነቅ..ሩቄ ላመል ነው። እሷጋ እስክደርስ ሀሳቤ እንዥርግ ነው..ዝንተ አለምን መሳይ። ተራምጄ እስክደርሳት፣ ተንጠራርቼ እስክነካት የፊት ለፊቴ ገጽዋ የምጻትን ያክል ይርቀኛል። አቤት ስወዳት! አለም የእሷን ያክል መደሰቻ አልሰጠችኝም። አለም በኩስተራው የምታውቀው ፊቴ እሷ ፊት ነው የሚፈገው። ሳቄ እሷ ፊት ነው የሚጀምረው። የምንም ነገር መጀመሪያዬ ናት..እሷን አልፌ፣ እሷን ተሻግሬ የምጀምረው ምንም የለኝም። ፊተኝነትና ኋለኝነት ሳያሸብሩኝ በመኖሯ ውስጥ አለሁ። በነፍሴ እርሻ ላይ አቆጥቁጣ ደስታና መከራዬ ሆና ትጠዘጥዘኛለች..እጠዘጠዝላታለሁም። በእሷ ያወኩት..ከእሷ የተማርኩት ብዙ እውነት አለኝ..ከእውነቴ አንዱ ምድር ላይ ደጋግሜ ብፈጠር የእሷን ያክል መደሰቻ አላገኝም የሚለው ነው።

እስካያት..ዛጎል መሳይ አይኖቿን እስክሳለማቸው ተቅበዝባዥ ነኝ። እስክነካት..የገላዋን አንድ ቦታ እስክስመው ረፍት የለሽ ነኝ። በውበቷ ገዳም..በነፍሷ አጥቢያ ውስጥ የተሸሸኩ ባህታዊ ነኝ። ከጽድቅ ሌላ.. ከአኮቴት ሌላ አመል የሌለኝ። ባለሁበት የትም ቦታ ላይ አለች። እንደ መልከ ማርያም እየደገምኳት.. የነፍሷን ሰዐታት እያነበነብኩት ካለሁበት ወዳለችበት እተማለው። አተማመሜ ያስደንቀኛል..ወዴትም ባልተራመድኩት የችኮላ ርምጃ ነበር የምፈጥነው። ወደ እሷ ስሄድ ዝግ ብዬ አላውቅም..ከእግሮቼ የሚፈጥኑ ብዙ ሀሳቦች አሉኝ..ከሀሳቤ የሚፈጥኑ ብዙ ህልሞችም።

ሳያት ለፈንጠዝያዬ ምድር አትበቃኝም..ለሳቄ.. ለፍንደቃዬ አለም ትጠበኛለች። ሳያት ቀለያት አይበቃኝም..በጋቴ እሰነዝረዋለው። በክንዴ እመትረዋለው። ሳያት ሰማይ የጸደይ መልክ ይጸንሳል። ሳያት ጀምበር ብርሀን ታረግዛለች፣ ጨረቃ ጸዳል ትለብሳለች። ሳያት ሌላ ነኝ...እንደዚህ ቀደሙ ደማቅ። ሳያት በእኔ ውስጥ የማይሆን የለም..ተፈጥሮ እውነት ስታ በእኔና በእሷ ውስጥ ልክ ትሆናለች። አለም ያላየችው ብዙ ተዐምር እሷን በማየቴ ውስጥ ይስተናግዳል።

እየሳኩ ሄጄ እየሳኩ እነካታለው። እያሰብኳት ሄጄ እያሰብኳት አቅፋታለው..እዋሀዳታለው። የክረምት ጠል እንደጠጣች የጸበል ዳር በለስ ልጃገረድ ፊቷ በፈገግታና በውበት ተዥጎድጉዶ ክንዴ ላይ ሲያርፍ ያን ነው ህይወት የምለው። ያን ነው መኖር የምለው። ያ ነው ማመስገኛዬ። ያ ነው በህይወቴ እንዳላጣው የምሰጋው አምሮቴ። ያን ከሺ ብርቅ ልቆ፣ ከሚሊዮን እድል ልቆ ወደ እኔ የሚቦርቅ..ወደ እኔ የሚንጠራራ ፊቷን ሳየው ህይወት ባልሰጠኝ፣ መኖር ባልቸረኝ ክብርና ማዕረግ ውስጥ እንደቆምኩ አስባለው።

አልጋው መሀል ላይ እንደተጋደመች የሚስቅ ፊቷን በሚስቅ ከንፈሬ እስመዋለው። ሊያቅፈኝ የሚንጠራራ እጇን ሊያቅፋት በተዘረጋ እጄ እቀበለዋለው። ስታየኝ የምትሆነው መሆን ሳያት ከምሆነው መሆን ጋር ይዛመድብኛል። እኔ ብቻ እንደማልወዳት፣ እኔ ብቻ እንደማላፈቅራት፣ እኔ ብቻ እንደማልሳሳላት፣ እኔ ብቻ እንደማልናፍቃት፣ እኔ ብቻ እንደማላስባት፣ እኔ ብቻ እንደማልጨነቅላት በምትሆነው መሆን እደርስበታለው። የማልስመው የሰውነት ክፍል የላትም..ከእሷ ጋር ስሆን እንደሳምኳት ነው። እሷም የምትስስተኝ አንዳች የላትም..ሁኜ እንዳልኳት ትሆንልኛለች።

ነፍሴ መረጋጊያዋ ናት። ፊቷ ላይ እልፍ አእላፍ የዝምታ ቅኔን ትቀኛለች። የእሷን ፊት እንደማየት፣ የእሷን ገላ እንደመንካት በምድር ደስታ የላትም። እግዜርንም በእሷ ያመሰገነችውን ያክል በምንም አላመሰገነችውም። ነፍሴ ለብዙ ነገር አሜን ብላ ታውቃለች፣ ለብዙ ነገር እጅ ነስታ ታውቃለች፣ ለብዙ ነገር ወደ ሰማይ አይታ ታውቃለች እንደ እሷ የሆነችበት ግን የላትም።

እጄን በጀርበዋ ውስጥ ሽቅሽቄ አነሳኋትና ክንዴ ላይ አሳርፋታለው..ደረቴ ላይ እጥላታለው። ጠረኗ ከአለም ይሰውረኛል። ከወንድነቴ ዘልቆ በነፍሴ እንጦሮጦስ ውስጥ ያርፋል። አለም የሌላት..ጺጋን ያስከነዳ የአንገት ስር ሽታ አላት። ከእሷ ውጪ የትም የማይሸት፣ የትም የማይጠርን መዐዛ። ከእሷ አንገት ውጪ፣ ከእሷ ገላ ውጪ፣ ከእሷ ቀሚስ ውጪ በየትም ቅዱስ ቦታ ላይ የማይገኝ ሽታ። ያን የገላዋን ጠረን ተዋሀድኩት። ደረቴ ላይ አስተኝቼ አስተዋልኳት..ንጹህ ናት.. ንጹህ ያልሆነ ምንም የላትም። አይኗን፣ ቅንድቧን፣ አፍንጫዋን፣ ጉንጬዋን ሁሉ ነገሯን እየነካካሁ እስማታለው። የምሆነው መሆን ያስቃታል። ፊቴ ላይ ትፈነድቃለች። ሳቋ ሳያስቀኝ ቀርቶ አያውቅም። አብሬአት እስቃለው..አብሬአት እፈነድቃለው። ንጹህ ያልሆነ ምንም የላትም ብያችሁ የለ? ሳቃም እንደ ገላዋ ንጹህ ነው። ደረቴ ላይ አስደግፌአት ንጹህ ሴትነቷን እንደፈለኩ እሆንበታለው። በንጽህናዋ ውስጥ ንጹህ ሆኜ እፈጠራለው። ያኔ ነፍሴ ክንፍ ያላት ይመስለኛል.. በደስታ የማትበርበት የለም።

ክንዴ ላይ ታቅፌ፣ ደረቴ ላይ ለጥፌ ሁሉ ነገሯን ሳምኩት። ስስማት ነፍሴ ውስጥ ጣይ ትወጣለች፣ ጀምበር ትፈነጥቃለች፣ በ ልቤ አደይ ያቆጠቁጣል.. መስከረምን እሆናለው። ግን ስሜአት አልጠግብም። ከንጹህ ሳቋ፣ ከንጹህ ፍንደቃዋ ተዋህጄ አረካም። ከአጠገቤ ሽሽት ስትል በረሀ ነኝ..።

በነፍሴ ሁሉም ቦታ ላይ ጽፌአታለው። በመንገዴ ሁሉም ቦታ ላይ አትሜአታለው። የሌለችበት ወንድነት የለኝም። ጉንጬዋ የቤተክሲያን ያክል፣ የካህን እጅ ያክል፣ የመስቀልን ያክል ያምረኛል። ፊቷ እንደ ብር ወለባ፣ እንደ አመልማሎ፣ እንደ ዘበናይ ፈርጥ ያምረኛል። ሳቋ የምስራቅ ደፌ ነው..የተስፋዬ መውጫ። እግዜርን አሜን እለዋለው..እግዜርን ተመስጌን እለዋለው..ክብርህ ይስፋ እለዋለው..በእሷ በስድስት ወር ህጻን ልጄ።

# ዓለም አቀፍ

## በኡጋንዳ እስካሁን 109 ሰዎች በኢቦላ ቫይረስ ተይዘዋል 30 ሞቶች ተመዝግበዋል

በኡጋንዳ መስከረም ላይ የኢቮላ ወረርሽኙ ከጀመረ አንስቶ 109 በቫይረሱ የተያዙ ሰዎችና 30 ሞቶችን መዝገባቸውን የኡጋንዳ የጤና ሚኒስቴር አስታውቋል። እስከ ሰኞ ዕለት ድረስ 15ቱ ሞቶች የተመዘገቡት በዋና መዲናዋ ካምፓላ ነው።በአገሪቱ ዋና መዲና ካምፓላ ውስጥ የአንድ ቤተሰብ አባላት የሆኑ ስድስት ሕጻናት በኢቦላ መያዛቸውን ባለሥልጣናት አስታውቀዋል።

ስድስቱ ሕጻናት በቫይረሱ ሊያዙ የቻሉት በኋላ ላይ በቫይረሱ ሕይወታቸው ያለፈ አንድ ዘመዳቸው በቫይረሱ ከተጠቁ አካባቢዎች መጥተው እነርሱ ጋር ካረፉ በኋላ እንደሆነ የጤና ባለሥልጣናት አረጋግጠዋል።የህክምና ባለሙያዎች ቫይረሱ ወደ ካምፓላ እንዳይዛመት ለመከላከል ለሳምንታት ጠንካራ እርምጃ እንዲወሰድ ሲጠይቁ ቆይተዋል።

ቫይረሱ ሕዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች በፍጥነት የሚዛመት ሲሆን ይህ 'ሱዳን ስትሬን' ተብሎ የሚጠራው የኢቦላ ቫይረስ እስካሁን ክትባት አልተገኘለትም።በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ የወረርሽኙ ማዕከል የሆኑት ሙቤንድ እና ካሳንዳ ወረዳዎች ከሌሎች አካባቢዎች ተለይተው እንዲቆዩ ተደርጎ ነበር።በአገሪቷ መስከረም ላይ ወረርሽኙ ከጀመረ አንስቶ የኡጋንዳ የጤና ሚኒስቴር 109 በቫይረሱ የተያዙ ሰዎችና 30 ሞቶችን መዝግቧል። እስከ ሰኞ ዕለት ድረስ 15ቱ ሞቶች የተመዘገቡት በዋና መዲናዋ ካምፓላ ነው።

የአገሪቷ ፕሬዚደንት ዮዌሪ ሙሴቪኒ የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት ከጤና ባለሙያዎች በቀላሉ ስለሚተላለፈው በሽታ ለሚሰጡት ቅድመማስጠንቀቂያዎች እርምጃ ለመውሰድ ዘገምተኛ በመሆናቸው አንዳንዶች ስጋታቸውን ገልጸዋል።የጤና ሚኒስትር ጄን ሩት አሴንግ፣ ሕዝብ በስፋት በሚንቀሳቀስባቸው ከተሞች አካባቢ የቫይረሱ ስርጭት ስጋት እንዳሳደረባቸው ተናግረዋል።

በዋና መዲናዋ በቫይረሱ መያዛቸው የተረጋገጠው ስድስቱ ሕጻናት ስምና እድሜ ማንነታቸውን ለመጠበቅ ሲባል አልተጠቀሰም።ይሁን እንጂ እነዚህ ሕጻናት የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች አለመዘጋታቸው ታውቋል።ሚኒስትሯ ዶክተር አሴንግ እንዳሉት በቅርቡ በቫይረሱ ሳቢያ ሕይወታቸው ካለፈው ሰዎች መካከል ታማሚዎችን ሲያክሙ በቫይረሱ የተያዙ ስድስት የጤና ባለሙያዎች ይገኙበታል።




ካምፓላ የአገሪቷ የንግድ ማዕከል ስትሆን የኢቦላ ቫይረስ በፍጥነት ከተዛመተ ወደ ሌሎች አገራት የመዛመት እድሉ ከፍተኛ መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

## ሩሲያ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለኝን አጋርነት ማጠናከር ቀዳሚ ትኩረቴ ነው አለች

በሩሲያ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቅድሚያ ከምንሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን ሁሉን አቀፍ አጋርነት ማጠናከር ነው ሲሉ የሀገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰርጌይ ላቭሮቭ አስታወቁ።

ሚኒስትሩ የሀገሪቱን ቀጣይ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲና ስትራቴጂ በተመለከተ በሰጡት መግለጫ "ቅድሚያ ሰጥተን ከምንሰራባቸው የውጭ ጉዳይ ቁልፍ ስራዎች መካከል ከአፍሪካ ሀገራት ጋር ያለንን ሁሉን አቀፍ አጋርነት ማጠናከር ነው" ብለዋል።



እ.አ.አ በ2019 ስትራቴጂካዊ በሆነ ውሳኔ በሶቺ የተጀመረው የሩስያ አፍሪካ ጉባኤ የሁለትዮሽ ግንኙነቱን የበለጠ ለማጠናከር የሚያስችል ሲሆን ሩሲያም ይህንን ለማሳደግ ትሰራለች ነው ያሉት።

በአለም አቀፉ መድረክም የአፍሪካውያን ድምጽ እንዲሰማ እንፈልጋለን ፤ በተለይ በአሁኑ ወቅት ለአለም ምጣኔ ሀብት ስኬት የአፍሪካ ሀገራት ሚና ከፍተኛ ነው ሲሉ አንስተዋል።

ለዚህም ባለፉት አስርት አመታት የአፍሪካ ሀገራት የሀገር ውስጥ ምርት 50 በመቶ ማደጉ ግልጽ ማሳያ ነው ብለዋል ላቭሮቭ በመልዕክታቸው።

ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አክለውም የሩስያና የአፍሪካ ግንኙት ወንድማማችነትን ባጠናከረና ሉዓላዊነትን ባከበረ መልኩ ተጠናክሮ ይቀጥላል ማለታቸውን ከኤምባሲው ድረ-ገጽ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ሩሲያ ከአፍሪካ አገራት ጋር ሰላምን በማስፈን፣ ቀጠናዊ ደህንነትን በማረጋገጥ እንዲሁም በሉዓላዊ ሃገራት ጣልቃ ገብነትን በመከላከል የሚሉ ነጥቦች ዙሪያ ትኩረት ሰጥታ እንደምትሰራ ከዚህ በፊት ማስታወቋ ይታወሳል።

ከዚህ በተጨማሪም ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማጠናከር እና የሰብአዊ መብቶች ትስስር የሚሉት ጉዳዮች የትኩረት ነጥቧ ውስጥ ተካተዋል።

# ስፖርት





## የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ቁጥር ወደ 54 አደገ

ቦጋለ አበበ

የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ቁጥር ከቀጣዩ የፈረንጆች አዲስ አመት ጀምሮ በሃያ አንድ እንደሚያድግ ታውቋል። የዓለም አትሌቲክስ በየአመቱ በተለያዩ የዓለማችን ከተሞች ከሚያካሂዳቸው ውድድሮች መካከል ከቤት ውጪ እንደ ዳይመንድሊግና የጎዳና ላይ ውድድሮች ተጠቃሽ ናቸው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የቤት ውስጥ ውድድሮችን የበለጠ በማነቃቃት ለሜዳ ተግባራት፣ ለአጭርና መካከለኛ ርቀት አትሌቶች የውድድር እድሎችን በማስፋት የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮችን በተለያዩ ከተሞች እያካሄደ ይገኛል። በዚህም ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የዓለማችን አትሌቶች ተጠቃሚ እየሆኑና ራሳቸውን በትልቅ መድረክ የማሳየት እድል እያገኙ ነው።

የዓለም አትሌቲክስ ይህን የቤት ውስጥ የዙር ውድድር የበለጠ በማስፋትም ከመጪው 2023 ጀምሮ ሃያ አንድ ተጨማሪ ውድድሮችን እንደሚያካሂድ አሳውቋል። ይህም በአጠቃላይ በአመት የሚያካሂዳቸውን ውድድሮች ቁጥር ወደ ሃምሳ አራት አሳድጎታል።

መካሄድ ከጀመረ ስምንተኛ አመቱን በመጪው 2023 የሚይዘው የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድር ውስጥ በሰባት ከተሞች የሚካሄዱ ውድድሮች የወርቅ ደረጃ ተሰጥቷቸዋል። የመጀመሪያው የዙር ውድድርም በመጪው ጥር መጨረሻ በጀርመን ካርልሹ እንደሚካሄድ ይጠበቃል።

የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ቁጥር በአጭር ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እድገት እያሳየ ይገኛል። በ2020 ሰባት ውድድሮች ይካሄዱ የነበረ ሲሆን በ2021 ወደ ሃያ አራት ማደግ ችሏል። በ2022 ደግሞ ሰላሳ ሦስት ውድድሮች የተካሄዱ ሲሆን በ2023 ወደ ሃምሳ አራት



ከ2023 ጀምሮ ሃምሳ አራት የዓለም የቤት ውስጥ የዙር ውድድሮች ይካሄዳሉ፣

ማደግ ችሏል።

የውድድሮቹ ቁጥር መጨመር ፉክክሮችን የሚያስተናግዱ በርካታ የዓለም ከተሞችን በስፋት ተደራሽ እንደሚያደርግ የዓለም አትሌቲክስ ገልጿል። በዚህም አስራ ዘጠኝ የተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች ውድድሩን እንደሚያስተናግዱ የተገለጸ ሲሆን ቀሪዎቹን ውድድሮች ደግሞ የደቡብ አሜሪካና ኤሽያ ከተሞች እንደሚያስተናግዱ ታውቋል።

በ2023 የውድድር አመት የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው ውድድሮች በተጨማሪ የብርና የነሐስ ደረጃ የተሰጣቸው በርካታ ውድድሮችም በተለያዩ ከተሞች ይካሄዳሉ። በነዚህ ውድድሮች ፉክክር የሚደረግባቸው ርቀቶችም የሚሰጣቸው ደረጃ በየአመቱ እንደሚቀያየር ተጠቁሟል።

በ2023 የውድድር አመት በተለያዩ ከተሞች ውድድሮች ሲካሄዱ የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው ርቀቶች መካከል የሴቶች ስልሳ ሜትር፣ስምንት መቶ፣ ሦስት ሺና አምስት ሺ ሜትሮች ይገኙበታል። በተመሳሳይ በሴቶች ምርኩዝ ዝላይ፣ ስሉስ ዝላይና አሎሎ ውርወራ ውድድሮችም በወርቅ ደረጃ እንደሚካሄዱ ታውቋል። በወንዶች መካከልም አራት መቶ፣ አንድ ሺ አምስት መቶ፣ ስልሳ ሜትር መሰናክል፣ ከፍታ ዝላይና ርዝመት ዝላይ በወርቅ ደረጃ ይካሄዳሉ።

በነዚህ ውድድሮች አትሌቶች ከተካፈሉባቸው ፉክክሮች ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡባቸው ሦስት ውድድሮች ተመርጠው ከተወዳደሩ በኋላ በአጠቃላይ ነጥብ ብልጫ ያገኘ አትሌት አሸናፊ ይሆናል። ለዚህም የአስር ሺ ዶላር ሽልማትና ከአስር ሺ በላይ ዩሮ ጉርሻ ተዘጋጅቶለታል።

የአጠቃላይ የዙር ውድድሩ አሸናፊዎች የገንዘብ ሽልማት እንዳለ ሆኖ በእያንዳንዱ የወርቅ ደረጃ ባለው ፉክክር ቢያንስ ሰባት ሺ ዶላር ሽልማት እንደ አጠቃላይ የተዘጋጀ ሲሆን አሸናፊ የሚሆን አትሌትም እስከ ሦስት ሺ ዶላር የሚያገኝ ይሆናል።

የብር ደረጃ በተሰጣቸው ውድድሮች በአጠቃላይ ከአርባ ሺ ዶላር በላይ የተዘጋጀ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ፉክክር አሸናፊ የሚሆን አትሌት ቢያንስ አራት ሺ ዶላር ተሸላሚ ይሆናል። የነሐስ ደረጃ በተሰጣቸው እያንዳንዱ ውድድሮች ደግሞ አጠቃላይ ከአስራ ሁለት ሺ ዶላር በላይ ሽልማት የቀረበ ሲሆን ለአንድ ውድድር አሸናፊ አትሌት ሁለት ሺ አምስት መቶ ዶላር ሽልማት ይበረከታል።

በተለያዩ የውድድር ዓይነቶች አሸናፊ የሚሆኑ አትሌቶች ከገንዘብ ሽልማት በተጨማሪ በ2024 ግላስጎ በሚካሄደው የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና በቀጥታ ተሳታፊ መሆኑን ያረጋግጣል።

የወርቅ ደረጃ ያላቸውን ውድድሮች የሚያስተናግዱት ከተሞች የጀርመኗ ካርልሹ ቀዳሚ ናት። በአሜሪካ ቦስተንና ኒውዮርክ፣ በፈረንሳይ ሌቪን፣ በስፔን ማድሪድ፣ በፖላንድ ቶረንና በእንግሊዝ በርሚንግሃም የሚካሄዱ ፉክክሮች የወርቅ ደረጃ የተሰጣቸው ሆነዋል።


### ማረሚያ

ረቡዕ ጥቅምት 9 ቀን 2015 ዓ.ም በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ገጽ 13 በሳምሶን ጌታቸው አስመጪ ስም በወጣው የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ የቲን ቁጥር 0038779252 ተብሎ የወጣው በስህተት ስለሆነ 0003551975 ተብሎ ተስተካክሎ ይነበብ፡፡

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከ ወረዳ 11 የቤት ቁጥር 9999/1 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0069735326 ሀሴታ መላ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማህበር ከተመዘገበኩበት ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ያልተሰራበት ቁጥር 0029 (አንድ ቅጠል) የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሀሴታ መሳ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 671 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0002001943 ታደለ ተስፋዬ ወ/ገብርኤል ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ የተሰራበት ከቁጥር 0001 እስከ 0928 እና ያልተሰራበት ከቁጥር 0929 እስከ 1000 የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ታደለ ተስፋዬ ወ/ገብርኤል**

### ለ3ኛ ጊዜ የወጣ የጥሪ ማስታወቂያ

የሳሚሊ ግላስ ወርክስ ኃላ.የተ.የግል ማህበር በጥቅምት 18 2014 ዓ.ም (ኦክቶበር 28፣ 2021) ባለአክስዮኖቹ በቃለጉባዔ ባስተላለፉት ውሳኔ መሠረት ድርጅቱ እንዲፈርስ መወሰኑ ይታውቃል። ከዚህም ጋር በተያያዘ ሕጋዊ የማፍረስ ሂደቱን ለማስኬድ ይቻል ዘንድ አቶ ኤርሚያስ አያሌው ቸርነትን እና ወ/ሪት ረድኤት እስጢፋኖስ ተካን በሂሳብ አጣሪነት መሾሙን በሃምሌ 3፣ 2014 (ጁላይ 10፣ 2022) እንዲሁም መስከረም 7፣ 2015 (ሴፕቴምበር 17፣ 2022) ቀን በወጡት አዲስ ዘመን ጋዜጣዎች ለሁለት ጊዜያት ያክል ማስታወቁ ይታወሳል። በመሆኑም ሳሚሊ ግላስ ወርክስ ኃላ.የተ.የግል ማህበር እዳ አለበት ወይም በእዳ እፈልገዋለሁ የሚል ማንኛውም ግለሠብ ወይም አካል በማህበሩ ላይ አለኝ የሚሉትን እዳ ወይም ተከፋይ ወይም ሌላ ማናቸውም ዓይነት ሕጋዊ አግባብነት ያላቸው የገንዘብ ወይም የተከፋይነት ጥያቄዎችን በተመለከተ ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በማዘጋጀት አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 03፣ልዩ ስሙ ወሎ ሰፈር አካባቢ ድሬደዋ ህንጻ 6ተኛ ፎቅ የቤት ቁጥር 404 በሚገኘው የሂሳብ አጣሪው አድራሻ ይህ ማስታወቂያ ከተገለፀበት በአንድ (1) ወር ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ እዳውን በተመለከተ ማስታወቂያው ከወጣ በአንድ (1) ወር ጊዜ ውስጥ ለንብረት አጣሪው ያላሳወቀ ማንኛውም አካል ለሚደርስበት ጉዳት ንብረት አጣሪው ኃላፊነት የማይወስድ መሆኑን በማክበር ያሳውቃል።

**የሳሚሊ ግላስ ወርክስ ኃላ.የተ.የግል ማህበር (በመፍረስ ሳይ የሚገኝ) ንብረት አጣሪ**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር 2ኛ ፎቅ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0058735887 ኤፍ ጂ ጋርመንት ኃላፊነቱ የተ/የግ/ማ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ሰሜን ምዕራብ አ/አ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ቁጥር 001 የተሰራበት እና ከቁጥር 002 እስከ 250 CASH RECEIPT VOUCHER ያልተሰራበት /VOID/ ከቁጥር 001 እስከ 007 የተሰራበት እና ከቁጥር 008 እስከ 250 ያልተሰራበት፣ CASH SALES INVOICE /VAT/ EXCISE ከቁጥር 001 እስከ 250 Credits Sales INVOICE / VAT/ EXCISE ያልተሰራበት ከቁጥር 001 እስከ 250 DELIVERY NOTE ያልተሰራበት ከቁጥር 001 እስከ 250 GOODS RETURN NOTE ያልተሰራበት 001 የተሰራበት እና ከቁጥር 002 እስከ 250 PURCHASE VOUCHER ያልተሰራበት ከ001 እስከ 008 የተሰራበት እና ከቁጥር 009 እስከ 250 WITH HOLDING TAX ON PAYMENT ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ሰሜን ምዕራብ አ/አ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ኤፍ ጂ ጋርመንት ኃላ/የተ/የግ/ማ**

### የስም ማስታወቂያ

**በከ አረገሙ ሃርከ ዋቀዮ አዱኛሌሳ ሚኒስትሪ (BEKE ARGEMU HAREKA WAKEYO ADUGNALESA MINISTRY)** የተባለ የሃይማኖት ተቋም ምዝገባ ለማድረግ ያመለከተ በመሆኑ በዚህ ስያሜ እና ዓርማ ተቃውሞ ያለው አካል ካለ በ10 ቀን ውስጥ ወደ የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እንዲቀርብ፡፡

**የኢትዮጵያ የወንጌል አማኞች አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር KO-15 የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0023140949 ሳምራዊት ጌታቸው ሲሳይ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ጉለሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፈቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ውስጥ ከቁጥር 0051 እስከ 0250 ያልተሰራበት እና የገንዘብ መክፈያ ደረሰኝ ከቁጥር 0051 እስከ 250 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ጉለሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሳምራዊት ጌታቸው ሲሳይ**

### አዲስ አበባ አስተዳደር

በአመልካች/ከሳሽ አዲስ ብድርና ቁጠባ እና በተጠሪ/ተከሳሽ እነ ደምሰው ደመቀ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከታች በዝርዝር የተቀመጡት ተከሳሾች:- 4ኛ አንተነህ ደገሙ፣ 5ኛ ድባቡ አስናቀ፣ 7ኛ ብዙአየሁ ጋሻው፣ 8ኛ ቴድሮስ ጌታቸው፣ 9ኛ መንግስቱ ተገኝ፣ 10ኛ ኤርሚያስ ቶማስ በ28/02/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በሬጅስትራር መልስ በጽሑፍ እንዲያቀርቡ እንዲሁም በ02/03/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በችሎት ለክስ መስማት እንዲቀርቡ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 2ኛ ፍ/ብሔር ችሎት አዟል፡፡ የከሳሽ/አመልካች ክስ ከሬጅስትራር ጽ/ቤት ከቀጠሮ ቀን በፊት ቀርበው እንዲወስዱ እናሳስባለን፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**